# ጥናት አንድ ሮሜ 1፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ወንጌል የሚለው ቃል በጣም ተደጋግሞ በዚህ ክፍል ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ሊጠቁምን የሚችለው ነገር፤ በዚህ መልዕክት ውስጥ ይህ ወንጌል የሚለው ሃሳብ ትልቅ ስፍራ እንዳለውና ትኩረት ሰጥተን ልንመለከተው እንደሚገባን ነው፡፡
2. ወንጌል በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ምንነት ላይ ያተኮረ የእግዚአብሄር እውነት ነው፡፡
3. ወንጌል በነብያት መጻህፍትና በቅዱሳን ተስፋ የተሰጠ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ይህ ቁጥር ወንጌል የሚባለው ነገር ከብሉይ ኪዳን ጋራ እንዴት ነው የሚዛመደው? አዲስ ነገር ነው ወይስ ከቀድሞውም የነበረ የእግዚአብሄር ሃሳብ ነው የሚለውን ይመልሳል፡፡ ይህም ጥያቄ ሊጠየቅ የሚችለው ምናልባትም ከአይሁድ ሊሆን እንደሚችል ይታወቃል፡፡
4. የሮሜ ሰዎች ለኢየሱስ እንዲሆኑ የተጠሩ ናቸው፣ በእግዚአብሄር የተወደዱ ናቸው፣ የተጠሩት ቅዱሳን ለመሆን ነው፣ የሚገኙትም በሮም ውስጥ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
5. ስለ እነዚህ ሰዎች የሚሰማው እምነታቸው ሲሆን በዘመናችን የምንሰማው ግን መከፈላቸውን መጣላታቸውን፣ የተሳሳተ ትምህርት ውስጥ መግባታቸውንና የመሳሰሉትን ነገሮች ነው፡፡
6. ከእነዚህ አነጋገሮች የምንረዳው ነገር ወንጌልን ከኢየሱስ ክርስቶስ ነጥለን ማየት እንደማንችልና ከኢየሱስ የተለየ ወንጌል ሊኖር እንደማይችል ነው፡፡
7. ወደ ሮም መሄድ የፈለገበት ምክንያት፡ መንፈሳዊ ስጦታን ሊያካፍላቸው፣ ከእነርሱ ፍሬን ያገኝ ዘንድ፣ እነርሱ በእርሱ እርሱም በእነርሱ እርስ በእርስ እንዲጽናኑ ነው፡፡ በእኔ አመለካከት የጳውሎስ እነርሱን ማጽናናት ብቻ ሳይሆን በእነርሱም ለመጽናናት መዘጋጀቱ ትልቅ ትምህርት ይሰጠኛል፡፡
8. ልናደርግ የምንፈልጋቸውም መልካም ነገሮች እንኳን በጸሎት የጌታን ፈቃድ መጠየቅ ይገባል፡
9. በ1 ተሰሎንቄ ላይ የምንመለከተው ሰይጣን የእግዚአብሄር ስራ እንዳይሰራ የሚከላከልበትን መንገድ ሲሆን በዚህ ክፍል ግን እግዚአብሄር በባሪያው ፈቃዱን ሲፈጽም ነው፡፡
10. ሀ) ወንጌል ለድነት የሚሆን የእግዚአብሄር ሃይል እንደሆነ ለ) በወንጌል የእግዚአብሄር ጽድቅ እንደተገለጠ ሐ) የእግዚአብሔር ጽድቅ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በእምነት እንደሆነ
11. እያንዳንዱ ተካፋይ ሃሳብ እንዲሰጥና እንዲወያዩ ይደረግ፡፡

# ጥናት ሁለት ሮሜ 1፡18-32 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ18-20 የምናያቸው ሶስት ባህርያቱ፡ ቁጣ፣ ዘለዓለማዊ ሐይሉና፣ መለኮታዊነቱ ናቸው።
2. በዓውደ ንባቡ መሰረት እውነት የሚለው ነገር ስለ እግዚአብሄር ፍጥረቱን ብቻ በማየትና በማስተዋል ሊታወቅ ስለሚችለው እውነት ማለቱ ነው። ከእኛ አንጻር ደግሞ እግዚአብሄር በቃሉ የገለጸልንን እውነት ሰምተንና ተረድተን ከተረዳን በኋላ ክፋትን ለመተው ካለመፈለግ የተነሳ ህሊናችንን ጸጥ አሰኝተን ያሰብነውን መፈጸም ማለጽ ሊሆን ይችላል።
3. እርሱን አለማክበራቸው ያስከተለባቸው፡ ሃሳባቸው ፍሬቢስ ሆነ፣ ልባቸው ጨለመ፣ ሞኞች ሆኑና የመሳሰሉት ከክፍሉ ብዙ ሊዘረዘር ይችላል። ሰዎቹ ሞኝ የተባሉበት ዋነኛ ምክንያት የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሄርን መፍራት ስለሆነ ያ ስለሌላቸው ሞኞች ናቸው።
4. በእነዚህ በሁለት ነገሮች መሃል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት እግዚአብሄርን አውቃለሁ ብሎ የሚናገር ሰው እንደ እግዚአብሄርነቱ ሊያከብረውና ሊያመሰግነው ይገባል።
5. አዎን! ቁ24ት የሚጀምረው ስለዚህ በማለት ቁ26 ደግሞ የሚጀምረው በዚህም ምክንያት በማለት አስቀድሞ ወዳሉት ቁጥሮች ስለሚጠቁሙን እነዚያ ምክንያቶቹ ሲሆኑ፤ ቁ28 ደግሞ በሃሳባቸው እግዚአብሄርን ማወቅ አይጠቅምም በማለታቸው ብሎ በግልጽ ይናገራል። አሳልፎ መስጠት የሚለው ሃሳብ በእነርሱ ላይ የነበረውን ወደ ጥፋት እንዳይሄዱ የሚከለክውን ጸጋ ወይም ጥበቃውን ከእነርሱ ላይ አነሳ ማለት ነው።
6. ቁ27 ላይ በግልጽ የማይገባ እያለ ወንዶች ከወንዶች፣ ሴቶች ከሴቶች ጋራ ግብረስጋ ግንኙነት እንደሚያደርጉና ይህ ደግሞ ቁጣውን እንዳመጣባቸው ይነግረናል።
7. ቁ21 እግዚአብሄርን ያውቁታል ግን አያከብሩትም አያመሰግኑትም፣ ቁ28 ደግሞ እግዚአብሄርን ማወቅ ጥቅም የለውም በማለት ራሳቸውን አሳምነውና እውነቱን በመካድ በራሳቸው መንገድ ለመሄድ ሰበብ መፈለጋቸውን እንመለከታለን።
8. ሌሎቹ ሁሉ ሃጥያቶች ሰዎቹ ራሳቸው ወስነውና ፈቅደው በራሳቸው ላይ የሚፈጽሙት ሲሆን ይህ በቁ32 ላይ ያለው ግን ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን የሚያበረታቱ ናቸው።
9. ጥናቱን የተካፈሉት ሁሉ ራሳቸውን የሚጠይቁትን ለራሳቸው የሚመልሱት ይሁንላቸው።

# ጥናት ሶስት ሮሜ 2፡1-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቁ1 መሰረት በሌሎች ላይ የሚፈርደው ይህ ሰው የሚፈርድበትን ነገር ራሱ የሚያደርግ ስለሆነ የሚያመካኘው የለውም፡፡
2. የእግዚአብሄር ፍርድ ትክክለኛና የማይቀር እንደሆነ እናያለን፡፡ የሰው ፍርድ ሁሉን አጣርቶ ሳያውቅ በትንሽ እውቀቱ ይፈርዳል፣ የሰው ፍርድ አድልዎ አያጣም..አንተ ጨምርበት፡፡
3. አይሁዳዊ ምዕራፍ አንድን ብቻ ቢያነብ የሚሰማው፡ እነዚህ ባለጌዎች ልክ ነው ይበላቸው፣ ይገባቸዋል፣ እንዲያውም ሲያንሳቸው ነው የሚል ይመስለኛል፡፡ ምዕ 2 ግን አፉን የሚያሲዘው አልጠራጠርም፤ ምክንያቱም ጥሩ ሰው ነኝ፣ ከሌላው በአካባቢዬ ካሉት ሰዎች ሁሉ እሻላለሁ የሚልበትን ነገር በሙሉ አስጥሎታልና ነው፡፡
4. የእግዚአብሄርን ትዕግሥትና ቸርነት ወደ ንስሃ እንዲመጡ መሆኑን ባለመረዳት ወደ በለጠ እንቢተኛነትና ሃጥያት ውስጥ ራሳቸውን እንዳደፋፈሩ ይታያል፡፡
5. እነዚህ ቁጥሮች የሚያስተምሩን እውነት እግዚአብሄር በፈርዱ እንደማያደላ ሲሆን ሃዋርያው የጠቀሰበት ምክንያት፡ አይሁድ ከአህዛብ ይልቅ ለእርሱ ቅርብ እንደሆኑ ስለሚያስቡና የነርሱን ያህል በእኛ አይፈርድም በማለት በተሳሳተ አስተሳሰብ ራሳቸውን እንዳያታልሉ ነው፡፡
6. ህግ ሳይኖራቸው ሀጥያት የሰሩ ያለህግ ይፈረድባቸዋል፣ ህግ እያላቸው ሀጥያት የሰሩ በህግ ይፈረድባቸዋል፣ ጻድቅ የሚባለው ህግን የሚሰማ ሳይሆን ለህጉ የሚታዘዝ ነው፡፡
7. ህሊናቸው ይመሰክርባቸው እንደነበረ፣ ሃሳባቸው ይከሳቸው እንደነበረ፣ ይከለክላቸው የነበረ የህግ ትዕዛዝ በልባቸው የተጻፈ መሆኑ ያን ጊዜ ጌ ታ ሲገለጥ ግልጽ ይሆናል፡፡
8. ይህንን ያለበት ምክንያት እነዚህ ሰዎች ስም ብቻ እንጂ ምግባራቸው ምንም አይሁዳዊነት እንደማይታይበት ስላወቀ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በህግ ይተማመናሉ፣ ከእግዚአብሄር ጋራ ባላቸው ግንኙነት ይኩራራሉ፣ የእውሮች መሪ፣ በጨለማ ላሉት ብርሃን፣ አላዋቂዎችን መካሪ፣ ለህጻናትም አስተማሪ ነን ብለው ስለራሳቸው ያስባሉ፡፡
9. በአንድ ቃል ይህ ክፍል ‹‹ግብዝነት›› ተብሎ ሊጠቃለል ይችላል፡፡ አንድ እየተናገርን ሌላ አይነት ህይወት ስንኖር ለእግዚአብሄር ስምና ለቤ/ክ መሰደቢያዎች እንሆናለን፡፡
10. ግርዘት በመንፈስ በልብ መገረዝ እንጂ የስጋ ነገር አይደለም፡፡ ይሁዲነት በውስጣዊ ማንነት፣ ግርዛትም በልብ የሚደረግ ስለሆነ እኛ የበረከቱ ከካፋዮች ነን፡፡

# ጥናት አራት ሮሜ 3:1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል እያነጋገረ ያለው አይሁድን ነው። እርሱ የአይሁድ ጥቅም ብሎ የጠቀሰው የእግዚአብሄር ቃል በአደራ መሰጠትን ነው። በሮሜ 9:4-5 ደግሞ ልጅ መሆን፣ መለኮታዊ ክብር፣ ኪዳን፣ ህግን መቀበል፣ የቤተ መቅደስ ሥርዓትና ተስፋ በተጨማሪነት ተዘርዝረዋል።
2. ማጠቃለያ አድርጎ በቁ9 ላይ ያቀረበው ሃሳብ አይሁድና አህዛብ እንደማይበላለጡና ሁሉም ሃጥያተኞች እንደሆኑ ነው። ተቃራኒነት የለውም፤ ምክንያቱም ቁ9 ሃጥያትን በተመለከተ የተሰነዘረ ሃሳብ ሲሆን ቁ1 ግን ከእግዚአብሄር በተሰጣቸው ነገር ላይ ያተኮረ ነው።
3. ‹‹እኛ›› ሲል አይሁዳዊያኑን ሲሆን ‹‹እነርሱ›› ሲል ደግሞ አህዛብን መሆኑ ነው።
4. ከሃጥያት በታች መሆን ማለት የሃጥያት ባሪያና ተገዥ መሆን ማለት ነው።
5. በመጀመሪያው ምዕራፍ የዘረዘራቸው ዕለት በዕለት በሚፈጸሙትን ክፉ ተግባሮች ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ክፍል ግን የሰውን ልጅ ሁሉ ማለትም አንዱን ከሌላ ሳይለይ የአዳም ዘር በመሆናችን ብቻ የወረሰውን ያንን የሃጥያት ባህርይ የተመለከተ ነው።
6. ያልሆኑትን/የለም በመባል የተጠቀሱት ሃሳቦች፡ ጻድቅ የለም፣ አስተዋይ የለም፣ እግዚአብሄርን የሚሻ የለም፣ በጎ የሚያደርግ የለም፣ የሰላም መንገድ አያውቁምና የእግዚአብሄር ፍርሃት የለም። በተቃራኒው የተነገሩት ደግሞ፡ ጉሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፣ ሽንገላን ያዘወትራሉ፣ በከንፈሮቻቸው የእባብ መርዝ አለ፣ አፋቸው ርግማንና ምሬት ሞልቶበታል፣ እግራቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣን ነው፣ በመንገዳቸው ጥፋትና ጉስቁልና ይገኛል የሚሉት ናቸው።
7. ይህ ያጠናነው ክፍል ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሄር አስተያየት ሲታዩ ሁሉም አንድም እንኳን ሳይቀር ሃጥያተኞች እንደሆኑ እንማራለን። ከዚህም የተነሳ የተገለጠው የእግዚአብሄር ማዳን ለሁላቸውም እንደሚያስፈልጋቸው እንረዳለን።
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ያካፍል።

# ጥናት አምስት ሮሜ 3፡21-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በሮሜ 3፡21 ላጥ እንደ ድልድይ ሆነው የሰፈሩት ሁለት ቃላት ‹‹አሁን ግን›› የሚሉት ናቸው፡፡
2. በዚህ ቁጥር ላይ ‹‹ከህግ ውጭ›› የሚለው አነጋገር በህግ ሥር ያልሆነ፣ ከህግ ጋራ ግንኙነት የሌለውና ከህግ ጋራ ያልተጣመረ ለማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጽድቅ ህግና ነብያት መመስከራቸው ይህ ጽድቅ ዛሬ እግዚአብሄር አዲስ የመጣለት ሃሳብ ሳይሆን ቀድሞም ይህ አሰራሩ የተለመደ አሰራር እንደነበረ ያመለክታል፡፡
3. ህግና ነብያት የመሰከሩለት ነው፣ ህግና ነብያት የመሰከሩለት ነው፣ ጽድቁ አሁን ተገልጧል፣ ጽድቁ የእግዚአብሄር ጽድቅ ነው፣ የሚገኘውም ኢየሱስን በማመን ነው፣ ይህ ጽድቅ ልዩነት አያደርግም፡፡
4. ቁ22-23 ልዩነት የለም ያለበት ምክንያት ይህ ጽድቅ የማያስፈልገው በራሱ ጻድቅ የሆነ ሰው እንደሌለ እግዚአብሄር ራሱ በ3፡9 ላይ ስለደመደመ ነው፡፡ የሰው ልጅ እግዚአብሄር ካሰበለት የክብር ሥፍራ የወረደውና ዝቅ ያለው በሃጥያት ምክንያት ስለሆነ እነዚህ ሁለቱ ሊገነጣጠሉ ስለማይችሉ ነው፡፡
5. የሃጥያት ደመወዝ ሞት ነው እንዳለው ሃጥያትን የሰራችን ነፍስ ሁሉ በሞት መቅጣት አለባት፡፡ ከአዳም ጊዜ አንስቶ ሰዎች ሃጥያትን እየሰሩ ነገር ግን በሃጥያታቸው ሳይሞቱ እስከ ክርስቶስ ጊዜ ድረስ በትዕግስት አቆይቶ ለሁሉ የሚሆነውን መስዋዕት ክርስቶስን ስለሁሉ ሃጥያት መስዋዕት አድርጎ በመስጠት እግዚአብሄር ጻድቅነቱንና ምህረቱን በአንዱ በኢየሱስ ሥራ አሳይቷል፡፡
6. ሮሜ 3፡27-31 ያለው ክፍል ሰው ሊድን የሚችለው በመገረዝ ወይም ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን በእምነት ብቻ እንደሆነ በግልጽ የሚያስተምር ክፍል ነው፡፡ ይህም ማለት የተገረዘም የሚድነው በእምነት ነው ያልተገረዘም የሚድነው በአንዱ በዚሁ በእምነት ነው ማለት ነው፡፡
7. ሕግ ቦታ ያጣል የሚለው አነጋገር አያስኬድም፤ ምክንያቱም ሕግ ቀድሞውንም ሰው በራሱ መዳን እንደማይችል ለማረጋገጥና ወደሚያድነው ለመጠቆም የተሰጠ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ህጉን እናጸናለን›› ዮሐ 5፡46 እንደምናየው ሙሴ የጻፈው ስለ ኢየሱስ መሆኑና እምነትም የሚጠቁመን ወደ ኢየሱስ ስለሆነ እምነት ህግን የሚያጸና እንጂ የሚሽር አይደለም፡፡
8. እያንዳንዱ የተማረውን ሃሳብ ለቡድኑ ያካፍል፡፡

# ጥናት ስድስት ሮሜ 4፡1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አብርሃም የጸደቀው በእምነት እንጂ በሥራ አለመሆኑ የሚፎክርበት ነገር አይኖረውም። ከዚህ የምንማረው ነገር ቢኖር እኛም የጸደቅነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ስለሆነ ልንፎክር ወይም ልንመካ የምንችልበት ምንም ነገር ሊኖረን እንደማይችል ነው።
2. በቁ4 ላይ ሥራ ተብሎ እየተጠቀሰ ያለው በጉልበት ተሰርቶ ደመወዝ ስለሚያስገኘው የሥራ ዓይነት ሲሆን ቁ5 ደግሞ ለደህንነት ሊሰራ ስለሚሞከረው ሥራ ነው። በ1ኛ  ተሰ ላይ ያለው ክፍል የሚናገረው በሮሜ 4፡4 ላይ ስላየነው ምግባችንን ለማግኘት ስለምንሰራው ሥራ ነው። በቁ5 ላይ አለመስራትን የሚያደፋፍረው ሃሳብ ግን ለደህንነታችን የምንሰራውን ሥራ ነው።
3. አብርሃምና ዳዊት በዚህ ክፍል የመጡበት ምክንያት አይሁዳዊ ሁሉ እነዚህን ሁለት ሰዎች ትልቅ የአክብሮት ሥፍራን የሚሰጣቸው በመሆኑና ተደማጭነታቸውም የጎላ በመሆኑ ነው። በተለይ ዳዊት ትላልቅ ተብለው የሚታዩትን ሃጥያቶች ያደረገ ሰው በመሆኑና በእግዚአብሄር ይቅርታ ብቻ እዚህ መድረሱ ለጸሐፊው ሃሳብ ግሩም ድጋፍ ይሆናል።
4. የአብርሃም የጸደቀበት ጊዜ ልዩነት የሚያመጣው፣ ከተገረዘ በኋላ ከሆነ የጸደቀው ግርዛቱ ጽድቁን እንዳስገኘ ሊያስቡ ስለሚችል የጸደቀው ከመገረዙ በፊት መሆኑን ማረጋገጥ አስፈለገ።
5. ምንም ተስፋ በሌለበት ማለት የአብርሃምም ሆነ የሳራ ዕድሜ ልጅ ሊገኝ ይቻላል ለማለት ከሚያስችለው እድሜ እጅግ ያለፉ በመሆናቸው ተስፋቸው የተሟጠጠ ነው። አብርሃም በሚታየው ተስፋ አለመኖር ሳይሆን ያመነው እግዚአብሔር ልጅ እሰጥሃለሁ በማለት የገባለትን የተስፋ ቃል ላይ ነበረ የቆመው። እኛም የምንቆመው እግዚአብሄር በተናገረው ቃል ሊሆን ይገባል።
6. አብርሃም በጭፍን ያሉትን ሁኔታዎች የካደ ሰው ሳይሆን የእርሱ እርጅናና የሳራም ደግሞ የመጸነስ አቅም አለመኖሩን እያወቀ ነገር ግን ከዚያ በላይ በተሰጠው የተስፋ ቃል ላይ ለመቆም ቁርጥ ውሳኔ አደረገ ማለት ነው።
7. በዚህ ክፍል መሰረት ኢየሱስ ለሃጥያታችን ይቅርታን ለማስገኘት እንደሞተና ከሞት የተነሳው ደግሞ እኛን ጻድቃን አድርጎ በእግዚአብሄር ፊት ለማቅረብ ነው።
8. ታመን አላመመኝም፣ ቸግሮኝ አልተቸገርኩም ማለት እምነት ሳይሆን ክህደት (ተጨባጭ ሁኔታን መካድ) ማለት ነው። አብርሃም ግን አርጅቶ አላረጀሁም፣ መውለድ የማይችል ሆኖ መውለድ እችላለሁ በሚል ራሱን የሚያታልል ሳይሆን የአምላኩን ታላቅነትና ኤልሻዳይነት በመገንዘብ ቃልኪዳኑንም ደግሞ ለዘለዓለም የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ መሆኑን አምኖ ነበረ።

# ጥናት ሰባት ሮሜ 5:1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሀ) ከእግዚአብሄር ጋራ ጠላትነት ቀርቶ ሰላም ተፈጥሯል። (የሃላፊ ጊዜ)
   ለ) አሁን በማናቸውም ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መግባት ተሰጥቶናል:(የአሁን ጊዜ)
   ሐ) እግዚአብሄር በገባልን ተስፋ ሀሴት እናደርጋለን። (የወደፊት)
2. ሀ) በተገባልን ተስፋ ቁ2 ለ) በመከራችን ቁ3 ሐ) በእግዚአብሄር በራሱ ቁ11
3. በመከራ ሐሴት ለማድረግ ለሰው ልጆች በአጠቃላይ አስቸጋሪ ነገር ነው። ቁ 3 «እናውቃለን» የሚለው ሃሳብ እንደሚያስረዳን መከራ የሚመጣበት ምክንያት ለገባው ሰው መከራ ሐሴት የሚደረግበት ነው። ይህ ማለት በመከራ ውስጥ ስናልፍ ደስተኞች እንሆናለን ማለት ላይሆን ይችላል፤ዕብ 12:11 ነገር ግን መከራውን ስናልፈው በውስጣችን የሰራውን ስለምናውቅ ሐሴት ማድረግ እንችላለን።ዕብ 12:11
4. መከራ ወይም መከራን በትዕግስት ማሳለፍ ብቻውን የተፈተነ ባህርይን አያስከትልም፤ ሁሉም አማኝ ከሚያልፍበት መከራ የተፈተነ ባህርይ ያተርፋል ማለት አይደለም ምክንያቱም ያላመኑ ሰዎች ለመከራ የሚሰጡት አይነት ምላሽ የሚሰጥ አማኝ ቁጥሩ ብዙ ነው። መከራውን በትዕግስት ጸንቶ በትዕግሥት የሚያሳልፈው ግን ያድግበታል ስለዚህም መከራው አልፎ ሲያየው ሐሴት ያደርጋል።
5. አንዳንዱ ሰው በንዴት፤ ሌላው በማጉረምረም፤ በማናቸውም መንገድ መውጫን በመፈለግ፤ በእግዚአብሄር ላይ በማማረር፤ ለምን በእርሱ ላይ ሊደርስ እንደቻለ በመጠየቅና በመሳሰሉት መንገዶች ያስተናግዳል። አማኝ ግን እግዚአብሄር የልጁን መልክ እንድንመስል እኛን ለመስራት የሚጠቀምበት መሳሪያ እንደሆነ ሊያይ ይጠበቅበታል።
6. አብዛኛውን ጊዜ በመከራና በሥቃይ ውስጥ ሲያልፉ የከበረውን ተስፋ ያስባሉ፤ ምክንያቱም ከዚህ ከሉበት ሁኔታ የመላቀቅን ነገር ሲያስቡና ተስፋ የሚሆን ነገር ሲፈልጉ መንፈስ ቅዱስ ልጆቹን ለማጽናናት ከዚህ ህይወት ባሻገር ያላቸውን የክብር ተስፋ በማስታወስ ልባቸውን ያሳርፋል።
7. የእግዚአብሄር ጠላቶቹ ሳለን አንድ ልጁን በመስጠት ፍቅሩን ከገለጠልን (ቁ6፤ቁ10) ይልቁን አሁን ጠላትነታችን ቀርቶ ወዳጆቹ ወይም ልጆቹ ከተባልን በኂላ (ቁ9፤10)ቁጣን በእኛ ላይ ያመጣል የሚለው አስተሳሰብ ለአዕምሮ የማይመች አመለከከት መሆኑን ይጠቁመናል።
8. የእያንዳንዱ የየራሱን መልስ ይስጥ።

# ጥናት ስምንት ሮሜ 5:12-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሐጥያት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም ገባ፤
   ሞት በሐጥያት በኩል ወደ ዓለም ገባ፤ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ በዚህ መንገድ ገባ፤
   ከህግ በፊት ሐጥያት ነበረ፤ ህግ ከሌለ ሀጥያት አይቆጠርም፤ ህግን ባልጣሱትም ላይ ሞት ነገሰ፡፡
2. ይህ ክፍል በየግላቸው ሰዎች ስለሚሰሯቸው ሃጥያቶች እንደማይናገር ልናውቅ የምንችለው በቁ 14 ላይ ከህግ በፊት የነበሩና ህግን ያልተላለፉ ሰዎች ላይ ጭምር ሞት በመንገሱ ነው፡፡ ይህ ክፍል የሚናገረው በአዳም ወደ ሰው ልጆች ሁሉ ስለተላለፈው ሃጥያት ነው፡፡
3. ኩነኔ(ሞት) የአንድ ሰው የሃጥያት ውጤት ነው፡፡ ስጦታው ሲመጣ ግን የአዳምን ሀጥያት ከመጋራታችንም አልፎ እያንዳንዱ ሰው ቁጥር ስፍር የሌለው አለመታዘዝን የጨመረበት ስለሆነ ለዚህ ሁሉ የሚያስፈልገው የፀጋ ስፋት መጠን የሚጠቁመን ነው፡፡
4. ሰዎች ሁሉ አልነገሱም ምክንያቱም የአዳም ሐጥያት መቀበል የሚጠይቅ ስላልሆነ ሰው የሆነ ሁሉ ያገኘዋል፡፡ ስጦታውን በተመለከተ ግን ቁ 17 እንደሚናገረው በእምነት መቀበል ስለሚጠይቅ የተቀበሉት ብቻ ናቸው በህይወት የሚነግሱት፡፡
5. ወረድ ብሎ በቁ 19 ላይ ተጠቅሶ የሚገኘውን የክርስቶስን ፍጹም መታዘዝ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
6. ለእኛም ትምህርት አለው፡፡ በአንደኛ ደረጃ በእኛ መታዘዝ ብዙዎች ሊባረኩ እንደሚችሉና ባለመታዘዛችንም ደግሞ ከእኛ አልፎ ሌሎች ሊጎዱበት እንደሚችሉ ያሳየናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር ምን ያህል አለመታዘዝን እንደሚጠላና መታዘዝን እንደሚያከብር እናያለን፡፡
7. ህግ በሌለበት ሀጥያት ሀጥያት መሆኑ ስለማይታወቅና(ቁ13) ህግ ሲመጣ ግን የሰውን ሃጥያተኛነት ስለሚገልጥ ነው፡፡ ሃጥያት በሞት እንደነገሰ ጸጋ ደግሞ በጽድቅ እንዲነግስ ነው፡፡ ቁ 21.
8. የተደጋገሙት ቃላት: ጸጋ፤ አብልጦ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ፤ መትረፍረፍ የሚሉት ሲሆኑ የተትረፈረፉት ደግሞ: ስጦታ፤ ፀጋና የጽድቅ ስጦታ፤ ፀጋ ናቸው፡፡
9. እያንዳንዱ የሚሰማውን የደስታ ሁኔታ የመናገር ዕድል ይስጠው፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ሮሜ 6:1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አስቀድሞ ባለው ምዕራፍ 5:20 ላይ ሐዋርያው የሰነዘረውን እውነት አስመልክቶ ሊነሳ የሚችል ጥያቄ ነው። የሐዋርያው መልስ በቁ 2 ላይ ይገኛል ይኸውም «ለሃጥያት ሞተናል ታዲያ እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?»
2. ጥያቄው «...ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?» የሚል ነው። ይህንን እውነት አለመረዳት ሃጥያት በእኛ ላይ እንደቀድሞው የበላይነት እንዳለው በመቁጠር የመገዛት ኑሮን እንዳይኖር ይህንን እውነት መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው።
3. የተጠመቅነው በመጀመሪያ ደረጃ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋራ አንድ እንድንሆንና ደግሞም በአዲስ ህይወት እንድንኖር ነው ይላል። ጥምቀት እያለ የሚናገረው በአንደኛ ደረጃ እርሱ ባለፈበት ሁሉ እኛም በእርሱ ውስጥ ሆነን በሞቱና በትንሳኤው የመሳተፋችንን መሳያ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን እውነት የምንመሰክርበት የውሃ ጥምቀትን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
4. በምድራዊ ፍርድ ቤት ተከሶ በሞት የተቀጣ ሰው ምውት ስለሆነና እዳውን ስለከፈለ ፍርድ ቤት ዳግመኛ እንደማይፈልገው እንዲሁም ለሀጥያት የሞተ ሰው ከሀጥያት ባርነት ነጻ ወጥቷል ማለት ነው።
5. ቁ 5 ላይ «ከእንግዲህ» በማለት የሚናገረው ከኢየሱስ ጋራ በሞቱና በትንሳኤው ከተባበርን በኋላ ያለውን ጊዜ ነው የሚያመለክተን።
6. «እንዲሁም» የሚለው ቃል በቁጥር 10 ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት የሆነውንና እየሆነ ያለውን ነገር በመንፈስ ቁዱስ አማከኝነት በአማኝ ህይወትም ተፈጻሚነት ሊኖር እንደሚገባ መናገሩ ነው። የተሰጣቸው መመሪያ ለሃጥያት እንደሞቱና ለእግዚአብሄር ህያዋን እንደሆኑ እንዲቆጥሩ ነው።
7. ሀ) በስጋቸው ሃጥያት እንዳይነግስ ለ) ብልቶቸውን የሃጥያት መሳሪያ አድርገው እንዳያቀርቡ ሐ) ራሳቸውን ለእግዚአብሄር እንዲያቀርቡ መ) ብልቶቻቸውን የጽድቅ መሳሪያ አድርገው ለእግዚአብሄር እንዲያቀርቡ፡
8. ፡እነዚህ ሁለት ቃላት በሥልጣን ላይ ያተኮሩ ናቸው። አማኝ ሃጥያት አይሰራም ማለት ሳይሆን (1ኛ ዮሐ 1:8) ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ቃላት እንደሚጠቁሙን ሃጥያት በአማኝ ላይ እንደቀድሞው የገዢና የተገዢነት ግንኙነት ሊኖረው አይችልም ማለት ነው።
9. የእያንዳንዱን የጥናት ተንፋይ የግል መልስ የሚስተናገድበት ጊዜ ይሆናል።

# ጥናት አስር ሮሜ 6:15-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የመጀመሪያው ማለት በ6:1 ላይ ያለው ጥያቄ ያተኮረው ሃጥያትን በመጨምርና እያበዙ በመሄድ ላይ ሲሆን፤ በቁ15 ላይ የተጠየቀው ጥያቄ ግን ያተኮረ የሚመስለው ሃጥያትን እንስራ ወይ የሚል ሃሳብ አለው::
2. ሐዋርያው እንደገለጸው ሀጥያት የሚሸነፈው በሞት እንጂ በህይወት በመኖር ስላልሆነ ከሃጥያት ጋራ ትግል መያያዝ መልስ እንደማይሆን ለመሳወቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሐጥያትን እያወቁ መስራት ተመልሰን በባርነት ቀንበር ውስጥ መያዝ እንደሆነ ማስረዳቱ ለጥቅማችን ስለሆነ ነው:: ገላ 5:1
3. ለሁለቱም ጥያቄን በመጠየቅ ነው መልሱን የሰጠው:: ጥያቄውም «አታውቁም ወይ» በሚል ማወቅ የሚገባቸው ነገር እንዳለ በማስገንዘብ ነው የመለሰው::
4. ሮሜ 6:15 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ የሰጠው የአማኝን ከሃጥያት ባርነት ተላቆ የመታዘዝ ባሪያ እንደሆነ በማስገንዘብ ነው::
5. በክፍሉ መሰረት ሰው ነጻ የሚወጣው ለሰማው ትምህርት በሙሉ ልብ በመታዘዝ ነው:: በዚህ ክፍል ትምህርት የሚለው ሃሳብ ከምዕራፍ 1 ጀምሮ የተነገረው የወንጌል እውነት ማለት ነው::
6. አማኝ በክርስቶስ ሲያምን ከሃጥያት ጋራ የነበረው የባርነትና የጌትነት ግንኙነት ቀርቶ ለጽድቅ ባሪያና ተገዥ አድርጎ ራሱን በውዴታ ለመስጠት ውሳኔ አድርጓል::
7. ይህ ክፍል ሊናገር የፈለገው በሀጥያታችን ዕለት በእለት እየጨመርንና እየባስን እንሄድ እንደነበረ፤ አሁንም በጽድቅ እለት በእለት እየጨመርንና እያደግን እንድንሄድ የሚያበረታታን ሃሳብ ነው::
8. በቁ16-19 ሐጥያት ባሪያ የማድረግ ችሎታ እንዳለው ይነግረናል(ገላ 5:1 ዮሐ 8:34):: ቁ20-21 ደግሞ ሐጥያት ከደረግነው በኋላ የሚያሳፍር ነገር እንደሆነ ስናይ በቁ21-23 ደግሞ ሀጥያት መጨረሻው ሞት እንደሚያስከትል እናነባለን::
9. እያንዳንዱ የጥናት ተከፋይ ሃሳቡን የሚገልጥበት ወቅት ይሆናል::

# ለመሪው የተዘጋጀ
# ጥናት አስራ አንድ (ሮሜ 7:1-6)

1. በትዳር ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ከዚያ ከትዳር ህግ ነጻ ሊወጣ የሚችለው ባል ወይም ሚስት ሲሞት መሆኑን ያስረዳናል::
2. ሐጥያተኛ ነህ ወይም ህግን ተላልፈሃል በማለት ሊኮንነውና ሊፈርድበት ይችላል ማለት ነው::
3. በሁለቱ ጥቅሶች መሃል ያለው ልዩነት አማኝ የሞተው በ6:11 መሰረት ለሀጥያት ሲሆን በ7:4 መሰረት ደግሞ የሞተው ለሕግ ነው:: በሌላ በኩል ግን የእነዚህ ጥቅሶች ተመሳሳይነት ከሀጥያትም ሆነ ከሕግ ነጻ መውጣት የሚቻለው በመሞት ብቻ መሆኑን ሁለቱም ጥቅሶች በግልጽ ያረጋግጡልናል::
4. እንደ መጀመሪያ ባል ሆኖ የቀረበው በቁጥር 4 መሰረት ሕግ ሲሆን ነጻ ለመውጣት ደግሞ ከሁለቱ የአንዱ መሞት ግድ ስለሆነ እኛ ለሕግ ሞተናል:: በሁለተኛ ባልነት በዚሁ ቁጥር ውስጥ ከሙታን ተነሳ የሚባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::
5. በዩሐ 4:23 እና በ2ኛ ቆሮ 3:6 እንደምናነበው በክርስቶስ ስናምንና መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ከደረ በኋላ እግዚአብሄርን የምናመልከውና የምናገለግለው ህግ ስለሚያዘን ሳይሆን ፍቅሩ ግድ ስለሚለን የፍቅር ምላሻችን መሆን ይኖርበታል::
6. የሞትነው ለእግዚአብሄር ፍሬ እንድናፈራ ነው ይላል:: ፍሬ መፍራት ስላለበት ጊዜ ሲናገር ደግሞ ከህግ ሥርዓት ውስጥ ወጥተን «ለእርሱ ለሌላው ሆናችሁ...» እንደሚል የክርስቶስ ከሆንን በኋላ እንጂ በህግ ውስጥ እያለን የምናፈራው ፍሬ አያስደስተውም::
7. እነዚህን ሁለት ቁጥሮች በማቀናጀት ስንመለከት እግዚአብሄር ከአማኝ ፍሬአማ የሆነ አገልግሎትን እንደሚጠብቅ እንመለከታለን:: እነዚህ ቁጥሮች አገልግሎትን አስመልክቶ የሚጠቁሙን ሁለት ዋና ዋና መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው:: በመጀመሪያ ደረጃ ለህግ መሞትን ሲጠይቅ በተጨማሪ ደግሞ አገልግሎቱ በአዲሱ መንገድ መሆን እንደሚኖርበት ይጠቁሙናል::
8. እያንዳንዱ ለየግሉ ይመልሳል ውይይት የሚያስፈልገው ከሆነ ትወያዩበታላችሁ::

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት አስራ ሁለት (ሮሜ 7:7-25)

1. ቁ7 ላይ «ሕግ በራሱ ሐጥያት ነውን?» ቁ13 ላይ «ታዲያ በጎ የሆነው ነገር ሞት ሆነብኝን?» ቁ24 ላይ ደግሞ «ከዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል?»
2. እንደ መስረቅ፤ መግደልና ሌላ አማልክት ማምለክ የመሳሰሉት ሰው ሁሉ ሊያያቸው የሚችላቸው ደግሞም በህብረተሰቡና በመንግስት ህግም ሳይቀር ተቀባይነት የሌላቸው ሲሆኑ ምኞት ግን የውስጥ ነገር ስለሆነ ከእግዚአብሄርና ከሰውየው በስተቀር ሰውም ሆነ ህብረተሰቡ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ሊያሳይበት የማይችለው ትዕዛዝ ነው።
3. «ቅዱስ» የተባለው ህግን ሰጪው እግዚአብሄር ቅዱስ ስለሆነ ነው።
   «ጻድቅ» የተባለው ለሁሉም ሐጥያት ላይ ሲፈርድ ያለ አድልዎ በጽድቅ ስለሆነና «መልከም» የተባለው ደግሞ ሰዎች ደህንነት እንደሚያስፈልጋቸው እንዲረዱ በማድረግ ወደ መሲሁ ስለሚመራቸው ነው።
4. «በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ፤ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም።» የሚለው መጠቅለያ ሃሳብ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል።
5. ሮሜ 7:15-17 ያለው ጳውሎስ ሊያደርግ የሚፈልገው ነገር እያለ የሚያደርገው ግን የማይፈልገውን ነው፤ ስለዚህም በገላቲያ ላይ የሰፈረውን ሃሳብ የሚያረጋግጥ ልምምድን ነው ክፍሉ በግልጽ የሚያሳየን።
6. «ከዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል?» የሚለው ጥያቄ የምዕራፍ ሰባትን ዋነኛ ሃሳብ የሚገልጽ ዋነኛ ጥያቄ ነው።
7. በመጀመሪያ ደረጃ ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው አሮጌው ሰዋችን ከእኛ ጋራ እንዳለ እንዲገነዘብ ማድረግ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በ7:4 መሰረት ለህግ እንደሞትን ማሳየት ሰለዚህም ጸሃፊው በምስጋና እንደጨረሰና ወደ አዲሱ የድል ምዕራፍ (8) እንደተሻገረ ለችግሩ እግዚአብሄር የሰጠውን መፍትሄ ከ8:1-4 በማሳየት ማስረዳት።
8. እያንዳንዱ የራሱን አስተያየት ይናገር።

# ለመሪው የተዘጋጀ
# ጥናት አስራ ሶስት (ሮሜ 8:1-11)

1. ስለኩነኔ ይህ ክፍል የሚመልሳቸው ነገሮች፡ ክርስቶስን ያመነ ኩነኔ እንደሌለበት፤ ከሃጥያትና ከሞት ህግ ነጻ ወጥተዋል፡፡ ለነጻነታቸው ዋነኛ ምክንያት የህይወት መንፈስ በውሰጣቸው ስለገባ ነው፡፡
2. ሀ) አማኝ ከሞት ህግ ነጻ ወጥቷል ለ) በህግ ለመመላለስ እስከሞከረ ጊዜ ድረስ መወደቁ አይቀሬ ነው ሐ) በመንፈስ እስከተመላለሰ ድረሰ ህጉን ለመፈጸም ጉልበት አለው፡፡
3. ቁ4 እንደሚናገረው ህጉ ሁሉ ሊፈጸም የሚችለው ክርስቶስን ባመነው በእኛ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በሥጋ መመላለስ ማለት ልብን በምድራዊ ነገር ላይ ብቻ ባተኮረ መንገድ የመመላለስ ህይወት ሲኖን በሌላ በኩል ደግሞ በመንፈስ መመላለስ ማለት መንፈሳዊ ነገርን ቅድሚያ በመስጠት ልብን በሰማያዊ ነገር በመሙላት መመላለስ ማለት ነው፡፡
4. በሥጋ ፍላጎትና በመንፈስ ፍላጎት ላይ ልብን የማድረግ ነገር ነው፡፡ የስጋን ነገር ማሰብ ሞት ሲሆን የመንፈስን ነገር ማሰብ ደግሞ ህይወት ነው፡፡
5. ከ5-8 ያለው ክፍል የሚያወዳድረው ያላመነንና ያመነን ሰው መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ቁ7 ‹‹ከእግዚአብሄር ጋር ጠበኛ ነው›› የሚለው በሮሜ 5፡1 ካለው ሃሳብ ጋራ ይቃረናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 8፡9 ‹‹እናንተ ግን›› በማለት ለአማኞች ማነገሩም ተጨማሪ መልስ ነው፡፡
6. ከእግዚአብሄር ጋራ ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሄር አይገዛም፤ እግዚአብሄርን ማስደሰት አይችልም፡፡
7. በዚህ ክፍል ‹‹እናንተ›› የሚለው አማኞችን ሲሆን፤ ላላመነ ሰው ዋነኛ ምልክት ሆኖ የተጻፈው ነገር ደግሞ የእግዚአብሄር መንፈስ በውስጡ መኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው፡፡
8. ክርስቶስ በውስጣችሁ እስካለ ድረስ የእግዚአብሄር አይደለሁም ብሎ ማሰብ እንደማይቻልና መነፈሱ በውስጣችሁ እስከሌለ ድረስ ደግሞ ምንም ዓይነት ሰዎች ቢሆኑ የእግዚአብሄር ነኝ ማለት እንደማይችሉ ለማረጋገጥ ነው፡፡
9. እያንዳንዱ የጥናት ተካፋይ የራሱን ሃሳብ ያካፍል፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት አስራ አራት (ሮሜ 8:12-27)

1. ሀ) የስጋን ስራ ለመግደል እንዲችል ሃይል ይሆነዋል።
   ለ) ይመራዋል።　　ሐ) አባ አባት ለማለት ያስችለዋል።
   መ) ልጅነቱን ከመንፈሱ ጋራ ይመሰክርለታል
2. አማኞች ከሞት ፍርድ ያመለጡ ስለሆነ ይህ ክፍል የሚናገረው ሞት ለዘለዓለም ከእግዚአብሄር የሚለየንን ሞት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የመንፈሳዊ እድገት መሞት፤ በውስጣችን እግዚአብሄር ያኖረው ራዕይ የመሞትና የመሳሰሉት ሊሆን ይችላል።
3. ቁ9፤ 10 እና 11 ላይ መንፈሱ በውስጣችን እንዳለ ያሳስበናል ስለዚህም ይህ ከሆነ በመንፈስ ፈቃድ መሄድን፤ በመንፈስ መመራትንና በመንፈስ የስጋን ስራ መግደልን የየእለት ተግባሩ አድርጎ አማኝ መመላለስ ይኖርበታል።
4. ይህ ቃል የሚያመለክተው ቀድሞ የነበርንበትን ሁኔታ ሲሆን ይህም የፍርሃት ባሪያዎች እንደነበርን ነው።
5. የክብሩ ተከፋይ የሆነ የመከራውም ተከፋይ ለመሆን ዝግጁ መሆን አሁን ባለንበት ህይወት መከራና ሥቃይ እንደሚኖርብን ከመከራ በኋላ ክብር እንዳለ መከራችንንና የሚጠብቀንን ክብር ማነጻጸር እንደሚጠቅም
6. መቃተት ማለት ከውስጥ የሆነ ከጭንቀትንና ከስቃይ ለመገላገል የሚደረግ ሲቃ የተሞላ ጪኸት ነው። በዚህ ምንባብ ውስጥ ፍጥረት ይቃትታል(22) አማኝ ይቃትታል(23) መንፈስ ቅዱስ ይቃትታል(26)
7. ዛሬ ልጅ አይደለንም ወይም ልጅ የምንሆነው ወደፊት ነው ማለት እንዳልሆነ ቁ14 ያረጋግጥልናል። ቁ23 የሚናገረው ይህ ሟች የሆነው ሰውነታችንም ሙሉ ለሙሉ ከሽታ፤ ከመበስበስና ከመሳሰሉት ነገሮች ነጻ ሆኖ ሙሉ የሆነውን ተስፋ የተገባልንን ቤዛነት የምንቀበልበትን ናፍቆት የሚያስረዳ ክፍል ነው።
8. በድካማችን ያግዘናል(26) እንዲሁም ለቅዱሳን ይማልዳል(26፤27)። መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ህይወት የሚያከናውናቸው ነገሮች፦
   ሀ) የሥጋን ስራ ለመግደል ያስችለዋል(13)
   ለ) ይመራዋል(14)　ሐ) አባ አባት ለማለት ድፍረት ይሰጠዋል(15)
   መ) የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ከመንፈሱ ጋራ ያረጋግጥለታል(16)
   ሠ) በድከሙ ያግዘዋል(26)　ረ) ሊገለጥ በማይቻል መቃተት ይማልድለታል(27)
9. የእያንዳንዱ የየራሱን መልስ መስጠጥ እንዲችል ማበረታታት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት አስራ አምስት (ሮሜ 8:28-39)

1. ለበጎ ይደረጋል የሚለው የሚያጠቃልላቸው፡ ሀ) እግዚአብሄርን የሚወዱትን ለ) እንደ ሃሳቡ የተጠሩትን ነው:: «ነገር ሁሉ» ሲል የማይጨምረው ነገር አይኖርም::
2. እግዚአብሄር ስለ አማኞች የወሰነው ውሳኔ የልጁን መልክ እንዲመስሉ ነው:: ለዚህም የወሰዳቸው እርምጃዎች:- ጠራቸው፤ አጸደቃቸው እንዲሁም አከበራቸው::
3. አማኝ ገና የሚከብር ሳይሆን በእግዚአብሄር አይን ከብሮ ያለቀለት ነገር ነው:: በተግባር ስናየው ገና መክበራችንን እንጠባበቃለን ይሁን እንጂ እግዚአብሄር ወሰነ ማለት ሆነ ማለት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል::
4. ዝርዝራቸው ግልጽ ስለሆነ እዚህ መዘርዘር አላስፈለገም:: «ለዚህ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከላይ የተዘረዘሩትን ራሱ አውቆ፤ ራሱ ወስኖ፤ ጠርቶ፤ አጽድቆ ለክብር የማብቃቱን ታላቅ ሥራ በማሰብ የመገረም ጥያቄ ነው::
5. ተቃዋሚ ወይም ከሳሽ የለንም ለማለት አይደለም፤ ምክንያቱም የወንድሞቻችን ከሳሽ የሚለው ዲያቢሎስና መላዕክቱ አሉ:: ነገር ግን ከሳሽ ቢመጣም ዳኛውና ፈራጁ እርሱ ራሱ ያጸደቀን ስለሆን ክሱ ውድቅ ነው ለማለት ነው::
6. መንፈስ ቅዱስም ሆነ ኢየሱስ የሚማልዱልን ከአለም እንድንወጣ ሳይሆን በአለም ሳለን እንድንጠበቅ ነው:: በአለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ አለምን አሸንፌዋለሁ ነው ያለው ኢየሱስ ሲናገር::
7. ዋነኛው ጥያቄ «ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው?» ቁ35 የሚለው ሲሆን መልሱ ደግም በቁ37 ላይ «ምንም አይለየንም» የሚለው ነው::
8. ተረዳሁ የሚለው እውነት አማኝን ከእግዚአብሄር ፍቅር ሊለየው የሚችል አንዳችም ነገር እንደሌለ ነው:: በቁ37-38 የተዘረዘሩት በአማኝ ዕለታዊ ህይወት ሊገጥሙት የሚችሉ ሲሆኑ በቁ38-39 የተዘረዘሩት ደግሞ ከዚያ ያለፉና እላይ ከተጠቀሱት የጠነከሩ የሚመስሉ ነገሮች ናቸው::
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ በመስጠት ተነጋገሩበት::

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት አስራ ስድስት (ሮሜ 1:1-8:39)

1. ጽድቅ ማን እንደሚያስፈልገው፣ የመጽደቂያው መንገድ ምን እንደሆነ፣ የጸደቀ ሰው የሚለማመዳቸው ነገሮችና የመሳሰሉትን የሚመልስ ሲሆን የጸደቀ ሰው ሊኖረው የሚገባውንም የህይወት አይነት ይህ መጽሀፍ በሰፊው ይነግረናል:: ከላይ የተዘረዘሩት ማለትም ጽድቅ የሚገኘውም ሆነ በጽድቅ መንገድ መመላለስ የሚቻለው ደግሞ በእምነት ብቻ እንደሆነ ስለሚያስተምር ሶስቱንም ዘርፎች ይጠቀልላል:: « ጻድቅ በእምነት ይኖራል::»
2. እግዚአብሄር ጻድቅነቱን ለመጠበቅ ሐጥያትን መቅጣት ነበረበት:: የሰው ልጆች ደግሞ በሃጥያታቸው እንዲጠፉ አልፈለገምና ስለዚህ እነዚህን ሁለት ነገሮች ለማድረግ ሃጥያት ሳይቀጣ እንዳይቀርና የሰው ልጆች ደግሞ ከሞት እንዲያመልጡ ልጁን መስጠት ነበረበት::
3. ጽድቅ በእምነት ብቻ መሆኑ ዘሬ እግዚአብሄር አዲስ የፈጠረው ነገር ሳይሆን ቀድሞም በብሉይ ኪዳን ዘመንም ቢሆን ጽድቅ በእምነት ብቻ እንደነበረ ለማረጋገጥ ነው::
4. ሀ) ከእግዚአብሄር ጋራ ጠላትነት ቀርቶ ሰላም ተፈጥሯል:: (የሃላፊ ጊዜ)
   ለ) አሁን በማናቸውም ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መግባት ተሰጥቶናል:(የአሁን ጊዜ)
   ሐ) እግዚአብሄር በገባልን ተስፋ ሀሴት እናደርጋለን:: (የወደፊት)
5. ሀ) ክርስቶስ ሲሞት እርሱም ከክርስቶስ ጋራ አብሮ መሞቱን ሊያውቅ ያስፈልጋል(ቁ3)::
   ለ) ለሃጥያት መሞት ብቻ ሳይሆን ራሱን ለእግዚአብሄር ህያው እንደሆነ መቁጠር (ቁ11)፤
   ሐ) ለእግዚአብሄር ህያው መሆኑን መቁጠር ብቻ ሳይሆን ለጽድቅ መሳሪያ አድርጎ ራሱን እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል::
6. በ6:15 ላይ የሚታየው ሰው ከህግ ነጻ መሆንን የሚያየው በሀጥያት ለመኖር ምቹ መንገድ እንደተገኘ አድርጎ ሲሆን፣ በ7:18 የሚታየው ሰው ደግሞ በሃጥያት ላለመኖር የሚችለውን ሁሉ ጥረት በራሱ የሚሞክር ነው:: የመጀመሪያው ሰው ችግር ሀጥያት ባሪያ የማድረግ ችሎታ እንዳለው አልተገነዘበም፣ ሌላው ሰው ደግሞ መልከም ማድረግም ሆነ ሃጥያትን ድል ማድረግ በራስ የማይቻል ነገር እንዳልሆነ ያልተረዳ ሰው ነው::
7. ምዕራፍ ሰባት በራስ ጥረት የሚሞከር ሙከራ ሁሉ ትርፉ ድከምና ተስፋ መቁረጥ እንደሆን ሲያሳይ ምዕራፍ ስምንት ደግሞ እግዚአብሄር መስቀሉን የመጽደቃችን መንገድ አድርጎ እንደሰጠን ቅድስናችንን አስጀምሮ የሚያስጨርሰንን መንፈስ ቅዱስን እንደሰጠን ያስተምረናል::
8. እግዚአብሄር ጽድቃችንን የጀመረ፣ ቅድስናችንን ከግብ የሚያደርስና ለመጨረሻ ክብር የሚያበቃን ብቻ ሳይሆን ከወደደን ከዚህ ከፍቅሩ እኛን መለየት የሚችል አንዳች ፍጥረት ሰለሌለ ተደላድለን ያለፍርሃት በሰፊው በፍቅሩ ውስጥ ለመኖር ያስችለናል::

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት አስራ ሰባት(ሮሜ 9:1-13)

1. ጳውሎስ ምዕ8ትን ሲጨርስ በሞቀ ስሜት ማለትም ከክርስቶስ ፍቅር ማንም ወይም ምንም ሊለየው እንደማይችል በማረጋገጥ ጨርሶ ምዕ9ኝን ሲጀምር በሥጋ ወገኖቹ ስለሆኑት ልቡ በሀዘን እንደቆሰለ በመናገር በሀዘን ስሜት ነው ምዕራፉን የከፈተው፡፡
2. በዚህ ክፍል በሐዋርያው ህይወት ውስጥ የሚታየው ትልቅ እውነት ሌሎች ወደ ዘለዓለም ህይወት እንዲመጡ ያለው ከልብ የሆነ ፍላጎት ግልጽ ሆኖ የሚታይ ሲሆን፣ የሰዎች መጥፋትም ልቡን ምን ያህል እንደሚሰብረው ማየት ይቻላል፡፡ ይህንን አይነት ልብ የሚታይበት ሌላው ሰው ሙሴ ነው፡፡ ዘጸ 32:32
3. ሀ) ልጅነት ዘጸ 4:22 ለ) መለኮታዊ ክብር ዘጸ16:10 ሐ) ኪዳን ዘፍ15:18 መ) ህግን መቀበል ዘዳ 5:1-22 ሠ) ቤተመቅደስና ተስፋ ረ) አባቶች ሰ) የክርስቶስ የስጋ ሐረግ ሮሜ1:3
4. የእግዚአብሄር ቃል ላለመሻሩ የሰጠው ምክንያት ‹ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለም› ከአብርሃም ዘር የሆነ ሁሉ ልጁ አይደለም፡፡ ማለትም ሮሜ2:28-29 እንደሚናገረው እስራኤላዊነትና የአብርሃም ልጅነት የውስጥ ነገር ነው፡፡
5. በቁ6-13 ከሌሎቹ የአብርሃም ልጆች በተለይም ከእስማኤል ይልቅ ለይስሃቅ የተስፋ ቃል እንደገባ እንዲሁም ከኤሳው ይልቅ ያዕቆብን እንደወደደ በመናገር እግዚአብሄር ቃሉን የማጠፍ ነገር እንዳልሆነ ያመለክተናል፡፡ በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የጋራ ሆኖ የሚገኘው ሃሳብ ድርጊቱ የምርጫ ጉዳይ እንደሆነና ከሰው የሆነ ነገር እንደሌለ ማየት ይቻላል፡፡
6. እስማኤልና ይስሃቅ ምንም እንኳን የአብርሃም ልጆች ይሁኑ እንጂ በእናት የተለያዩ ናቸው፡፡ የኤሳውንና ያዕቆብን ሁኔታ ስንመለከት ግን ከአንድ እናት ሲሆኑ ከዚያም አልፎ መንትያ መሆናቸው፣ ገና ሳይወለዱ መሆኑና መልካምም ሆነ ክፉ ሳይሰሩ መሆኑ ነው፡፡
7. ይህ አነጋገር የማበላለጥን ሃሳብ እንጂ የጥላቻን ነገር የሚያስተምር አይደለም፡፡ ይህንን ሃሳብ ለመረዳት የሚከተሉትን የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍሎች ማጥናት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ማቴ 6:24፣ ሉቃ 14:26፣ ዮሐ 12:25
8. የእግዚአብሄርን ቃልኪዳን ያለመረዳታችን ጉዳይ እንጂ የተስፋ ቃሉ መሻር እንዳልሆነ ሊያስረዳቸው ነው፡፡ እኛ ደግሞ በሮሜ 8 መጨረሻ ከእግዚአብሄር ፍቅር የሚለየን የለም የተባለውን እውነት እስራኤል የተስፋ ቃል ኖሮት ከተጣለ የእኛም አስተማማኝ ሲሆን አይችልም የሚለውን ጥያቄ ይመልስልናል፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት አስራ ስምንት (ሮሜ 9:14-23)

1. እያንዳንዱ ያሰበውን ጥያቄ እንዲናገርና በቁ14 እና 19 ከተጠየቁት ጋራ አወዳድሩት።
2. ምህረቱ ቁ15፣ ርህራሄው ቁ15፤ ቁጣ ቁ22፤ ትዕግስት ቁ22፤ ባለጠግነቱ ቁ23 ሲሆን ከሁሉ ጎልቶ የሚታይ የምህረቱ ጉዳይ ነው። ቁ15፤ 16፤ 18፤ 23
3. የቁ14ት ጠያቂ ራሱንም ጨምሮ የሚጠይቅ ይመስላል ስለዚህ አማኞች በትክክለኛ መንፈስ የሚጠይቁት ጥያቄ ከመምሰል ሌላ በደንብ መልስ ተሰጥቶበታል። በሌላ በኩል ቁ19ን የጠየቀው ደግሞ ትህትና የጎደለው አይነት ሲመስል መልሱም ሳይመለስለት ዘለፋ ነው ያገኘው።
4. የፈርዖንን ልብ እንዲያደነድን በማድረግ የሃይሉ ማሳያና የስሙ መነገርያ አድርጎ ሲጠቀምበት ሙሴን ደግሞ በምህረት በመሸከም ለራሱና ለህዝቡ መዳን ምክንያት አድርጎታል። በሁለቱም እግዚአብሄር ክብሩን ለመግለጥ ተጠቅሞባቸዋል።
5. እሱ ራሱ ከሆነ ወሳኝ ለምን በእኛ ላይ ያላክካል? ለጥያቄው እርሱ የጠበቀው ዓይነት መልስ የተሰጠው አይመስለኝም እንዴያውም ተግሳጽ እንጂ መልስ ሆኖ አላየውም። በአጭሩ ንግግር ‹‹ልክህን እወቅ›› ነው የተባለው።
6. እግዚአብሄር የወደደውን ማድረግ ችሎታ ብቻ ሳይሆን መብትም እንዳለው ያስተምረናል።
7. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ እንዲሰነዝር እድል ይሰጠው።

# <u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>

## <u>ጥናት አስራ ዘጠኝ (ሮሜ 9፡23-33)</u>

1. ከአህዛብ የተወሰኑና ከአይሁድም እንደዚሁ የተወሰኑ ሲሆን የተጠሩበት ምክንያት ደግሞ የክብሩ ባለጠግነት እንዲታወቅ ነው ይላል።
2. ቁ25-26 የሚናገረው ስለ አህዛብና ስለ አይሁድ ነው (ኤፌ 2፡12)። ክፍሉ ሊናገር የሚፈልገው ሃሳብ እግዚአብሄር ምንጊዜም ቢሆን የመረጣቸው ቅሬታዎች እንደሚኖሩት የሚጠቁመን ነው።
3. ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች 25-26 ሊያስተላልፉ የፈለጉትን ሃሳብ ነው ይህም ክፍል በማጠናከር የሚናገረው ማለትም እግዚአብሄር እስራኤል በቁጥር ብዙ ቢሆንም ሁሉም ቅሬታ አይደሉም። እግዚአብሄር ደግሞ በራሱ ምርጫ ቅሬታን ይጠቀማል ነው ሃሳቡ።
4. ምህረት ለሮጠ ወይም ለወደደ አይደለም ከሚምር ከእግዚአብሄር ነው እንጂ የሚለወን የሚያጠናክር ሲሆን ጽድቅን በእምነት እንድንከተል የሚያደርገን እንኳን የእርሱ ቸርነት እንደሆነ እንማራለን።
5. ሁለቱ ዓይነት ሰዎች አህዛብና አይሁድ ናቸው። ልዩነታቸው ደግሞ አህዛብ ጽድቅን አልፈለጉም፤ አይሁድ ፈልገዋል፤ አህዛብ ሳይፈልጉ አግኝተዋል፤ አይሁድ ፈልገው አላገኙም።
6. የእግዚአብሄር ምርጫ ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም አዚህ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ለማግኘት በእምነት መከታተል እንጂ በሥራ ሊሆን የማይችል ነገር እንደሆነና አለቱ የሆነውን የሚያምን አይሁድም ሆነ አህዛብ እንደማያፍር ይነግረናል።
7. ምዕ 9 በሙሉ እግዚአብሄር የገባውን ቃል ኪዳን የማያጥፍ አምላክ መሆኑንና በፍጥረቱ ላይ ደግሞ ሙሉ መብት ያለው መሆኑን የሚናገር ሲሆን ይህ ክፍል ደግሞ ቅሬታን በማስቀረት ፈቃዱን ማከናወኑ አስቀድሞ በነብያቱ ያወጀው ነገር እንጂ አዲስ ነገር እንዳልሆነ ያሳያል።
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይግለጥ።

# ስመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሃያ (ሮሜ 10:1-8)

1. ስለ ህዝቡ አንድ ምኞት እንዳለው ይህም ምኞቱ ደህንነታቸው እንደሆነና ለዚህም በጸሎት በእግዚአብሄር ፊት እንደሚያቀርብ ይናገራል። ለህዝባችን ከስጋዊ ችግር በፊት ለደህንነታቸው ማልቀስ እንደሚኖርብን ያስተምረናል።(እስራኤላዊያን ስጋዊ ጥያቄ ስላልነበራቸው አልነበረም)
2. የሚያድነውን መምረጥ የእግዚአብሄር ፈንታ ሲሆን ከልብ የሆነ ጸሎት ማድረግና የወንጌልን እውነት መናገር ግን የእኛ ሃላፊነት መሆኑን መማር እንችላለን። 2ኛ ጢሞ 2:10
3. ጳውሎስ በአገልግሎቱ በተለማመደውና በተመለከተው ስለ እነዚህ ሰዎች መናገር የሚችል ሲሆን ከዚህ በላይ ግን እርሱ ራሱ ለእግዚአብሄር ከነበረው ቅንዓት የተነሳ ቤ/ክ አሳዳጅ መሆኑ ለዚህ ራሱ ተጨባጭ ምስክር ነው።
4. ቅንዓታቸው እውቀት የጎደለው ስለሆነ ሊጠቅማቸው አልቻለም። እውቀት አጡ ማለት የእግዚአብሄር ጽድቅ የሚገኝበትን ትክክለኛ መንገድ እንጂ በህግ ውስጥ የሰፈረውን ህግጋት ማወቅ ማለት አይደለም፤ የኦርቶኮክስን ሃይማኖት ስናይ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል።
5. ከእግዚአብሄር የሆነውን ጽድቅ አላወቁም እንዲሁም የራሳቸውን ጽድቅ ለመመስረት ፈለጉ።
6. ሁለት አይነት ሲሆኑ እነዚህም በህግ የሚገኝና በእምነት የሚገኝ ተብለው ተጠቅሰዋል።
7. በህግ የሚገኘው ጽድቅ ህጉን ሁሉ መፈጸም የቻለ በህይወት ይኖራል(ይጸድቃል) ሲለን በእምነት የሚገኘው ግን ሰማይ መውጣት ምድር መውረድ ወይም ምንም ዓይነት ስራ ሳይሆን በእምነት እግዝአብሄር የሚሰጠውን ጽድቅ መቀበል እንደሆነ ያስተምረናል። ቁ6-7 ክርስቶስ ከሰማይ እንዲወርድ ወይም ከሞት እንዲነሳ ያደረግነው ነገር የለም ሁሉ ያለቀለትና እግዚአብሄር ራሱ የሰራው ስለሆነ የእኛ ድርሻ በእምነት መቀበል ብቻ ነው።
8. ሁሉም የግሉን መልስ ይሰጣል።

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሃያ አንድ (ሮሜ 10፡9-21)

1. ኢየሱስ ጌታ ነው ብሎ በአፍ መመስከርና እግዚአብሄር ኢየሱስን ከሙታን እንዳስነሳው ማመን ያስፈልጋል፤ በኢየሱስ ያመነ ሁሉ አያፍርም፤ ደህንነትን በተመለከተ በአይሁድና በአህዛብ ልዩነት የለም፤ የጌታን ስም የሚጠራ ማንኛውም ሰው ይድናል።
2. ዝም ብሎ በአፍ ‹‹ኢየሱስ ጌታ ነው›› የማለት ነገር ሳይሆን ከልብ የእርሱን ጌትነት መቀበልና ለጌትነቱ ለመገዛት ፈቃደኛነትን የመግለጥ ጉዳይ ነው። ለአይሁድ ይህንን ማለት የኢየሱስን አምላክነት የመቀበል ጉዳይ ሲሆን ለአህዛብ ደግሞ ከቄሳር በላይ የሆነ ጌታ አለ ማለት ስለሆነ በዚያን ዘመን ይህንን ለማለት መፍቀድ ከልብ የሆነ ለውጥን የሚጠይቅ እውነት ነው።
3. ኢየሱስ ብሎ መጥራት ቢሆን የእርሱን ስም በክፉም በደግም ጠርቶ የማያውቅ አይገኝም። ነገር ግን ስሙን መጥራት ሲባል ይህ ስም ሊያድነኝ የሚችል ከማንኛውም ስም የበለጠ የተለየ ስም እንደሆነ በማመን መጥራት ማለት ነው።
4. ሀ)ስሙን የሚጠራ ይድናል ለ)ስሙን ለመጥራት ማመን ያስፈልጋል ሐ)ለማመን መስማት ያስፈልጋል መ)ለመስማት የሚናገር(ሰባኪ) ያስፈልጋል ሠ)ለመስበክ መላክ ያስፈልጋል ረ)የሚሰሙ ሁሉ ያምናሉ ማለት አይደለም።
5. ሰዎች የጌታን ስም ጠርተው እንዲድኑ ማመን ስላለባቸው ለማመን ደግሞ መስማት ስለሚያስፈልግ ወንጌልን ላልሰሙት ሁሉ የማሰማት ትልቅ አደራ ተጥሎብናል። የሚናገር ደግሞ መላክ ስላለበት ክርስቶስ ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንገልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ በሚለው ቃል ተልዕኮ ተቀብለናል። ወንገልን ተናገርን ማለት ግን የሰሙን ሁሉ ያምናሉ ማለት ስላልሆነ ባይቀበሉንም ተስፋ ባለመቁረጥ መናገር እንደሚኖርብን እንማራለን።
6. በምዕራፍ 9 ውስጥ እግዚአብሄር በሉዓላዊነቱ የወሰነው ነገር እንዳለ ያስተማረን መንፈስ ቅዱስ ራሱ ደግም በዚህ በምዕራፍ 10 ውስጥ ሰዎች ለመዳን ወንገልን መስማት እንደ ሚያስፈልጋቸውና ወንገልን ሰምተው የዳኑት ሰዎች ደግሞ ላልሰሙት የመናገር ሃላፊነት እንዳለባቸው ስለተናገረን ልንታዘዘው ይገባናል።
7. እያንዳንዱ በየግሉ የተማረውን በየተራ ያካፍላል።

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሃያ ሁለት (ሮሜ 11፡1-15)

1. ጳውሎስ እርሱ ራሱ እስራኤላዊ ስለሆነና አንድ ምስክር ሆኖ ሊጠቀስ እንደሚችል ሲናገር በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሄር ማንም የለም ተብሎ በታመነበት በኤልያስ ዘመንም የእርሱ የሆኑ ቅሬታዎች እንደነበሩት በማስገንዘብ እግዚአብሄር በማናቸውም ዘመን ቅሬታዎች እንደሚኖሩት ያስተምረናል።
2. ኤልያስ የሚታየው ከእርሱ በስተቀር በእስራኤል እግዚአብሄርን የሚያመልክና የሚያገለግል ሰው የለም፤ ነበር ግን እግዚአብሄር ብቻ የሚያውቃቸው ብዙዎች እንዳሉ ያሳስበዋል።
3. በቁ1 እና በቁ11 ላይ ባሉት ሁለት ጥያቄዎች መሃል ያለው ልዩነት ቁ1 የሚጠይቀው ከእግዚአብሄር አንጻር እግዚአብሄር ጥሏቸዋል ወይ ሲሆን ቁ11 ግን እነርሱ ራሳቸው የተሰናከሉትና የማይመለሱት በቋሚነት ነው ወይ ማለት ነው።
4. እግዚአብሄር በዚህ ክፍል እስራኤልን ለመመለስ የተጠቀመበት መንገድ አህዛብን በማዳን አይሁድን ማስቀናት ነው። እነርሱ ሲለፉለት የነበረውን ደህንነት ምንም ቦታ ያልነበራቸው አህዛብ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ሲያገኙ ማየት ወደ ልባቸው ይመልሳቸው ይሆናል።
5. በእነዚህ በሁለት ቁጥሮች ውስጥ የጋራ የሆነው ሃሳብ እስራኤልን ወደ ደህንነት ለማምጣት እግዚአብሄር የተጠቀመበትን ዘዴ ሐዋርያውም እየተጠቀመ እንዳለ እናያለን፣ ይኸውም እነርሱን ማስቀናት የሚለው ሃሳብ ነው።
6. ለአህዛብ የተሰጠውን አገልግሎቱን በትጋት ሲሰራ ብዙ አህዛብን ለወንጌል ምርኮ ያደርጋል ነገር ግን በሌላ መንገድ ደግሞ ከራሱ አነጋገር እንደምንረዳው ይህንን አብዝቶ ባደረገ ቁጥር የእርሱ ወገኖች የሆኑት አይሁድን በማስቀናት የማዳን ዕድል ደግሞ አለው።
7. እስራኤል እግዚአብሄር ወዳሰበላቸው ሥፍራ መመለስ በጳውሎስ አመለካከት ለአለም ሁሉ ትልቅ በረከት እንደሆነና የሞተ ሰው ከሙታን የመነሳቱን ያህል ተአምር ሆኖ ሊታይም እንደሚችል ያስገነዝበናል።
8. አብርሃም ባለመታዘዝ ለአህዛብ የበረከት ምንጭ እንደሚሆን እንዳላሰበ ግልጽ ነው። ከዚህ በማስከተል የቀረበው ጥያቄ ግን እያንዳንዱ የየራሱን የተማረውን የሚያካፍልበት ጊዜ ይሰጠውና ያካፍል።

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሃያ ሶስት (ሮሜ 11፡16-36)

1. በዘኍ 15፡19-21 እንደምናየው ለእግዚአብሄር የሚሆነው የእህል ቁርባን በመጀመሪያ ከወጣ በኂላ ነው የተቀረው ሁሉ የተቀደሰ የሚሆነው፤ ስለዚህም ከአጠቃላዩ ቡኾ ውስጥ አስቀድሞ ለእግዚአብሄር የሆነው ሲሰጥ የተቀረው ቡኾ ሁሉ የተቀደሰ ይሆናል ማለት ነው፡፡
2. በቁ13 ላይ እንደምናየው ለአህዛብ ነው የሚናገረው፡፡ ይህ ቁጥር አህዛብ በመሰረቱ የበረሃ ወይራ እንጂ የትክክለኛው ወይራ ዛፍ ቅርንጫፎች እንዳለሆኑ፤ አሁን ትክክለኛው የወይን ዛፍ ውስጥ በመግባት የበረከት ተካፋይ እንደሆኑና፤ በትክክለኛዎቹ ቅርንጫፎች ላይ ሊኩራሩ እንደማይገባቸው ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸው እንመለከታን፡፡
3. በእምነቱ የተስፋ ቃል ከእግዚአብሄር የተቀበለው አብርሃም ሲሆን እኛን አህዛቦችን ይሸከማል የሚልበት መንገድ የአህዛብም መባረክ የሚገኝበት መንገድ ለእርሱ በተገባለት ቃልኪዳን የተጠቃለለ ስለሆነ ነው፡፡
4. እስራኤላውያን  ከግንዱ ላይ እንደተሰበረ ቅርንጫፍ ሆነዋል፤ ይህም የሆነው ካለማመናቸው የተነሳ ነው፡፡ አህዛብ በእምነት ከግንዱ ጋራ ተጣብቀዋል፤ ይሀም በፍርሃት እንዲኖሩ እንጂ እንዳይኩረሩ፤ እግዚአብሄር ለአይሁድም ለአህዛብም እንደማያዳላ እናያለን፡፡
5. ‹‹የሆንከውን የሆንከው በእግዚአብሄር ቸርነት የተነሳ ስለሆነ አትኩራራ››
6. ምስጢር የተባው የእስራኤል በድንዳኔ ውስጥ መሆን ጊዜያዊ መሆኑና አህዛብ ወንጌልን ከተቀበሉ በኂላ ቃል ኪዳን ያለው እስራአል ሁሉ እንደሚድን ነው፡፡ ይህንን ማወቅ ለአህዛብ ጠቃሚነቱ የእግዚአብሄርን አሰራር እንዲረዱና በተለይም በትዕቢት እንዳይመላለሱ ይረዳል፡፡
7. ወንጌልን በተመለከተ የወንጌሉን መልዕክት ባለመቀበላቸው ከእግዚአብሄር ጋራ ጠበኞች ሲሆኑ፤ ምርጫን በተመለከተ ግን በአብርሃም በኩል የተመረጡ ስለሆኑ የተወደዱ ናቸው፡፡ ቁ29 ላይ ያለው ቃል በልቤ የሚያመጣው ስሜት እግዚአብሄር የሰጠኝ ደህንነቴም ሆነ ማናቸውም ስጦታ በድካሜ ምክንያት የማይወሰድ እንደሆነ ስለማይ በውስጤ የደስታ ስሜትን ያመጣል፡፡
8. ጳውሎስ በዚህ ክፍል ታላቅ በሆነ የአክብሮትና የአምልኮ መንፈስ ውስጥ እነዳለ እገምታሁ፡፡ ለተቀጥያው ጥያቄ እያንዳንዱ ለራሱ የተረዳውን እንዲያካፍል ጊዜ ይሰጠው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ (ማጠቃለያ ጥናት)

# ጥናት ሃያ አራት (ሮሜ 9፡1-11፡36)

1. አህዛብን መቀበሉ ህዝቡን ጣለ ማለት እንዳልሆነ በቁ6 ያስረዳል። ይህንንም ያለበትን ምክንያት ሲያስረዳ፤ ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ ወይም ደግሞ ከአብርሃም መወለዳቸው ልጆቹ እንደማያደርጋቸው ነገር ግን የተስፋ ቃል የተገባለት ይስሃቅ እንደሆነ ያስረዳል። (ከእስራኤል ውስጥ የተለየ እስራኤልን ነው እግዚአብሄር የተመለከተው።)
2. ሰዎች የተለያዩ ጥቅሶችን ሊያቀርቡ ነጻነት አላቸው። ጥቅሱን ከነ ምክንያቱ ጋራ እንዲያስረዱ ማበረታታት ያስፈልጋ።
3. የእግዚአብሄር በሉዓላዊነቱ የሚምረውን የመማርና ለሚራራለትም የመራራት መብት እንዳለ ሆኖ የሰው ልጆች የደህንነት መንገድ አድርጎ እግዚአብሄር ያዘጋጀውን ኢየሱስን በማመን ብቻ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንደሚኖራቸው ራሱ የደነገገ ስለሆነ ሚስጢሩን ሙሉ ለሙሉ አሁን ባንረዳውም ማን ተመረጠ ማን አልተመረጠም ሳይል ለፍጥረት ሁሉ የወንጌልን የምስራች ማወጅ የእኛ ሃላፊነት ነው።
4. እግዚአብሄር በዘመናት ሁሉ የሚሰራው በቅሬታ እንደሆነ ያስተምረናል። ይህንንም ለማሳየት የተጠቀመው የኤልያስን፤ ጳውሎስንና በአሁኑ ዘመንም ቅሬታዎች እንዳሉት ያሳያል።
5. እስራኤላውያን አሁን ያሉበት ሁኔታ እንዳያታልለንና ልባችን የትዕቢትን ነገር እንዳያስብ ያስተምረናል። ቁ18 እግዚአብሄር እነርሱን ከጣላቸው/ካልራራላቸው ለእኛ የሚራራበት ምክንያት የለውም፤ እግዚአብሄር የሰውን ፊት አይቶ አያደላምና።
6. ምዕ 9 የተስፋ ቃሉን በትክክል አለመረዳታችን እንጂ የተስፋ ቃሉ ተሽሯል ማለት እንዳልሆነ ይነግረናል ምክንያቱም ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤላዊ አይደለምና። ይህም ማለት የተስፋ ቃሉ በይስሃቅ በኩል እንደሚፈጸም እግዚአብሄር ራሱ የወሰነው ነገር ሲሆን ለምን ብሎ ለሚጠይቀው ደግሞ ‹‹የምምረውን እምራለሁ ለምራራለትም እራራለታለሁ›› በማለት የመምረጥና ያለመምረጥ መብት እንዳለው በማስረገጥ ይነግረናል። ወደ ም10 ስናልፍ ደግሞ እርሱ በሉዓላዊነቱ የደህንነት መንገድ ምን መሆን እንዳለበት ወስኗል፤ ይኸውም ሰው ሁሉ ወንጌልን በመስማት ሰምቶም በማመን ከእርሱ ጋራ እንደሚታረቅ ሲሆን ያመኑት ላለመኑት የማሰማት ሃላፊነት እንዳለባቸውም ይነግረናል። ም11 ሲገባ ደግሞ እስራኤል ይህንን መንገድ ስላልተቀበሉት ድንዛዜ ውስጥ አሉ፤ ይህ ማለት ግን አለቀላቸው ማለት አይደለም። በዘመናት ሁሉ ቅሬታዎች እንደነበሩት አሁንም አሉት፤ እግዚአብሄር የተስፋ ቃሉ ሙሉ ለሙሉ የሚፈጸምበት ጊዜና እስራኤል ሁሉ የሚድንበት ጊዜ ቅርብ እንደሆነ በማስረዳት ይጨርሳል።

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሃያ አምስት (ሮሜ 12፡1-8)

1. በዚህ ክፍል እያነጋገረ ያለው ‹‹ወንድሞች›› ስለሚል አማኞችን ነው፡፡ የሚነግራቸውም ነገር ሰውነታቸውን መስዋዕት አድርገው ለእግዚአብሄር እንዲያቀርቡ ነው፡፡ ርህራሄ በማለት የሚናገረው በምዕራፍ 1፡1-11፡36 ውስጥ እግዚአብሄር አደረገልን በማለት የተናገራቸውን ነገሮች በሙሉ ነው፡፡
2. መስዋዕቱ ህያው እንዲሆን፤ ቅዱስና እግዚአብሄርም ደስ የሚሰኝበት አይነት መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን መስዋዕት የተለየ የሚያደርገው አቅራቢው ራሱ መስዋዕት የሚሆነው መሆኑ፤ የመስዋዕቱ ዓይነት ሰው መሆኑ፤ እና መስዋዕቱ የማይሞት ህያው መሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡
3. በአጭር አነጋገር የእግዚአብሄር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለይተን እናውቅ ዘንድ ነው፡፡ ፈቃዱን ለማወቅ የእግዚአብሄርን ፊት በጸሎት ከመፈለግ አልፎ ቃሉን መመርመርና የተገለጠ ፈቃዱ ምን እንደሆነ  ከቃሉ መመርመር የአማኝ ሃላፊነት እንደሆነ እንማራለን፡፡
4. ራስን ከፍ በማድረግ ሌላውን አሳንሶ ማየት የዚህ ዓለም አስተሳሰብ ስለሆነ ስለራሳችን ትክክለኛ አስተሳሰብ እንዲኖረን በአዕምሮ መታደስ መለወጣችን የግድ አስፈላጊ ነው?
5. አንደኛው በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ብልቶቻችን በሙሉ አንድ አይነት ተግባር እንደሌላቸው ነው፡፡ የዚህ መንፈሳዊ ምሳሌነቱ ክርስትያኖች ብዙ ብንሆንም አንድ አካል አለን፤ ሁላችንም በአካሉ ውስጥ የተለያየ ስራ አለን፡፡
6. ሀ) ስጦታችን የተለያየ ነው ለ) ስጦታው በነጻ የተቀበልነው ነገር ነው ሐ) የተዘረዘሩት ሥጦታዎች በሙሉ ተግባርን የሚጠይቁ ስለሆኑ በስራ ላይ ማዋልና መጠቀም ይጠበቅብናል፡፡
7. በጣም እስማማሁ፤ ምክንያቱም አገልግሎት ሆነ አኗኗራችን በአስተሳሰባችን ትክክለኛነት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ትክክለኛ አመለካከት ከሌለን ትክክለኛ ኑሮ ሊኖር አይችልም፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ በነጻነት እንዲያካፍል ጊዜ ይስጠው፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሃያ ስድስት (ሮሜ 12፡9-21)

1. የቆሮንቶስ ሰዎች የኢየሩሳሌምን ቅዱሳን እንረዳለን ብለው የገቡት ቃል እነዲሁ ጳውሎስ እንዲሰሙላቸው በግብዝነት ለይስሙላ የተናገሩት መሆኑን ወይም ከፍቅር በመነጨ ልብ መናገራቸውን ማረጋገጥ ነው የፈለገው፡፡
2. ተዋደዱ፤ ተከባበሩና ተስማሙ የሚሉት ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይግለጽ፡፡
3. አማኝ አንድ ብቻውን ሆኖ ይህንን ትዕዛዝ ሊፈጽም የሚችልበት መንገድ የለም፤ ስለዚህም ከአንድ በላይና የአማኞች በአንድነት መሆንን የሚጠይቅ ትዕዛዝ ነው፡፡
4. ጌታን ለማገልገል በመንፈስ የጋሉ እንዲሆኑና ከአገልግሎት ትጋት ወደኋላ እንዳይሉ ያበረታታቸዋል፡፡
5. በተስፋ ደስ መሰኘት፤ በመከራ መታገስና በጸሎት መጽናት ሲሆኑ፤ በአገልግሎት ተስፋ በሚቀረጥበት ሰዓት ተስፋችንን እያሰብን በመደሰት የውስጥ ተስፋችንን እናድሳለን፤ ከመከራ ብዛት የተነሳ ተስፋ ለሚቆርጥ ደግሞ በትዕግስት ማሳለፍን ሲመክር በጸሎት መጽናት ደግሞ በማናቸውም ወቅት ለአማኝ ሃይሉን የሚያድስበት ዋነኛው መንገድ ነው፡፡
6. አንዱ ለተቸገሩ ቅዱሳን ካለን ማካፈል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንግድነት መቀበል ነው፡፡ ልዩነታቸው አንዱ በውጭ ሲሆን ሌላው ግን እቤታችን አስገብተን የምንረዳው ነው፡፡ በውጭ መርዳት ለብዙዎቻችን እንደሚቀለን አስባሁ፡፡
7. ክፉ ላደረጉብን ሰዎች እኛ መልሰን ክፉ ብናደርግባቸው እነርሱም አስቀድመው ካደረጉን የከፋ ነገር ለማድረግ ይገደዳሉ፤ ለክፋታቸው መልካምን በማድረግ ብንመልስ ግን ምናልባትም ወደልባቸው ይመለሳሉ፤ ይህ ባይሆን እንኳን መልሰው ለማጥቃት የሚኖራቸው ፍላጎት ይከሽፋል፡፡
8. እያንዳንዱ ተሳታፊ የራሱን መልስ ይስጥበት፡፡

## ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሃያ ሰባት (ሮሜ 13፡1-7)

1. በቀል የእኔ ነው ያለው እግዚአብሄር ራሱ ባስቀመጣቸው ባለስልጣኖች ተጠቅሞ መልካሙ እንዲመሰገን ክፉ አድራጊው ደግሞ እንዲቀጣ ሊያደርግ የሚችልበት መንገድ እንዳለው ይጠቁመናል፡፡
2. ሰው ሁሉ ለባለሥልጣን መገዛት እንዳለበት፤ ስልጣን ከእግዚአብሄር ብቻ ይሰጣል፤ ዛሬ ያሉት ባለሥልጣናት ሁሉ ከእግዚአብሄር ናቸው፤ በባለሥልጣን ላይ ያመፀ በእግዚአብሄር ላይ እንዳመፀ ነው፤ በባለሥልጣን ላይ ያመፀ በራሱ ላይ ፍርድ ያመጣል፡፡
3. መልካምን ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ቁጥር 3
4. የመጀመሪያው መልካም የሚያደርጉትን ማመስገን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ክፉ የሚያደርጉትን መቅጣት ነው፡፡
5. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሶስት ጊዜ የተሰጣቸው ስም ‹‹የእግዚአብሔር አገልጋዮች›› ነው፡፡ የእኛንና የእነርሱን አገልግሎት የሚለየው እኛ አውቀንና ፈቅደን የምናደርገው ሲሆን የእነርሱ ግን በአብዛኛው ሳያውቁትና ያለፈቃዳቸው ማገልገላቸው ነው፡፡
6. ሰዎች ለባለሥልጣን ሊገዙ የሚችሉባቸው ሁለት መንገዶችን ይጠቁመናል፡፡ የመጀመሪያው የሚመጣብንን ቅጣት በመፍራት (ሰውን በመፍራት) መገዛት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከህሊና የተነሳ ማለትም እግዚአብሄርን በመፍራት መገዛት ናቸው፡፡ ከፍርሃት የተነሳ ብቻ ሳይሆን ከህሊና የተነሳ እንድንገዛ ያደፋፍረናል፡፡
7. ግብር መክፈል እንዳለብን፤ ቀረጥ መክፈል እንዳለብን፤ መፈራት ለሚገባው መፈራትንና ክብር ለሚገባው ደግሞ ክብርን እንድንሰጥ ይጠበቅብናል፡፡
8. እነዚህ ሶስቱም እግዚአብሄር የመሰረታቸው ተቋማት ናቸው፤(ዘፍ 2፡18፤ ማቴ 16፡18፤ ሮሜ 13፡1) ሶስቱም ስለመሪዎቻቸው ነው የተነገረላቸው፤ ሶስቱም ለመሪው መገዛት እግዚአብሄር የሚያዘው እንደሆነ ያረጋግጣሉ፡፡
9. ሃሳቡን ለማካፈል ለሚፈልግ ሁሉ አጠር አጠር ያለ ጊዜ በመስጠት ሃሳባችሁን ተቀያየሩ፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሃያ ስምንት (ሮሜ 13፡8-14)

1. አንደኛው የፍቅር ዕዳ ለሰው ሁሉ እንዳለብን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምንም አይነት ዕዳ ከፍቅር በቀር እንዳይኖርብን ያስተምረናል።
2. ሁል ጊዜ መከፈል ያለበት የፍቅር ዕዳ እንዳለበት ሰው መመላለስ ያለበት አማኝ ሲሆን፤ እንዲወድ የተነገረው ደግሞ ሁሉንም ሰው ነው፤ ጥቅሱ የሚናገረው ስለ ባልንጀራ ስለሆነ ሰውን ሁሉ ያመነንና ያላመነን ሁሉ ይጨምራል።
3. ምክንያቱም ሰው ባልንጀራውን እንደራሱ አድርጎ ከወደደ በህግ ውስጥ አታድርግ የሚላቸውን ነገሮች ሁሉ ለማድረግ ያ የፍቅር ልቡ አይፈቅድለትም፤ ማለትም ከማድረግና ካለማድረግ ሳይሆን ከፍቅር የተነሳ ማለት ነው።
4. ይህ ቃል የሚጠቁመው/የሚያመለክተው ባልንጀራን መውደድ የሚለውን ሃሳብ ነው።
5. ሀ) ከእንቅልፍ የሚነቃበት ጊዜ አሁን እንደሆነ ያውቃ፤ ለ) መዳኑ ካመነበት ጊዜ ይልቅ ዛሬ ወደ እርሱ እንደቀረበ ያውቃል፤ ሐ) ሌሊቱ ሊያልፍና ቀኑ ሊጀምር እንደሆነ ይረዳል።
6. የጨለማን ሥራ መጣልና የብርሃንን ጦር እቃ መልበስ፤ በአግባብ መመላለስ፤ ጌታ ኢየሱስን መልበስ፤ የሥጋን ምኞት ይፈጽም ዘንድ ለሥጋ አለመገዛት።
7. ይህ ክፍል የሚናገረው ላልተፈቀደልን ነገር የምናሳየው መጓጓትና ፍላጎት እንጂ ምግብ፤ መጠጥና እረፍትን የመሳሰሉት ነገሮች እንዳልሆነ በቃሉ እነዚህን ነገሮች ወደ እግዚአብሄር እንድንጸልይና እንድንጠይቀው ተነግሮናል።
8. የፍቅርን ህይወት ለመኖር ፍቅር የሆነውን ክርስቶስን ካለበስነው የትም መድረስ አንችልም፤ በዮሐንስ ወንጌል ላይ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም እንደተባለው የምንሞክረው ሙከራችን ሁሉ ከንቱ ልፋት ይሆንብናል።
9. እያንዳንዱ የየራሱን መልስ ይሰጥበታል።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሃያ ዘጠኝ (ሮሜ 14፡1-12)

1. ይህ ክፍል የሚያጠቃልለው ከቁ1 እንደምንመለከተው አከራካሪ የሆኑትን ነገሮች ነው። እያንዳንዱ ሃሳቡን በመስጠት በደንብ ተወያዩበት።
2. ይህ ክፍል የሚያስተምረው ስለምግብ አበላል ሳይሆን እርስ በእርስ ስላለመፈራረድና እርስ በእርስ ስላለመናናቅ ነው። ይህንንም ከቁ3 ማየት እንችላለን።
3. ሀ) እግዚአብሄር ተቀብሎታል ለ) የእኛ አገልጋይ ስላልሆነ ሐ) ጌታ ሊያቆመው ስለሚችል
4. እያንዳንዱ በጌታፊት በተረዳው እውነት እንዲመላለስ የተፈቀደለት በቁ1 ላይ እንደምናነበው አከራካሪና አሻሚ በሆኑ ነገሮች ላይ ብቻ ነው። ቃሉ በግልጽ በሚናገርባቸው ነገሮች (አትስረቅ፤ አታመንዝር፤) ሁላችንም የመታዘዝ ሃላፊነት አለብን።
5. በእምነቱ ደካማ ሲል በክርስቶስ ያለውን ነጻነቱን ገና ያልተረዳና ምግብና ቀናትን የማክበር ነገር ለአማኝ ምንም ማለት እንዳልሆነ ያልገባው ማለቱ ነው።
6. እኛ ሰዎች ሁላችን እኩል እንደሆንና አንዳችን ከሌላችን እንደማንበልጥ በሁላችንም ላይ ለመፍረድ ሥልጣንና መብት ያለው እግዚአብሄር ብቻ እንደሆነ ለማሳየት ነው ሲሆን፤ እኛ የፈረድንባቸው ነገሮች ሁሉ ያንጊዜ ቦታ እንደማይኖራቸው እናያለን።
7. እያንዳንዱ የራሱን መልስ ይስጥበት።

# ለመሪው የተዘጋጀ

## ጥናት ሰላሳ (ሮሜ 14፡13-23)

1. ስለዚህ ሲል በቁጥር 12 ላይ የተናገረውን በሁሉ ላይ ሊፈርድ ላለው ለእግዚአብሄር የፍርድን ነገር እንድንተውና እርስ በእርስ እንዳንፈራረድ ለመናገር ነው፡፡
2. አማኝ መፈራረዱን ማቆም ብቻ ሳይሆን የማሰናከያ ድንጋይ ወይም ወጥመድን ላለማስቀመጥ ለራሱ ውሳኔ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት ወንድማችን ወይም እህታችን የሚሰናከሉበት ከሆነ ላለማድረግ ራሳችንን መግታት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡
3. ቁርጥ ሃሳብ ወይም ውሳኔ አድርግ ሲል፤ ውሳኔዎቻችን ሁኔታዎቹ ሲፈጠሩ ሳይሆን አስቀድመን ወንድሜን ወይም እህቴን የሚያሰናክል ነገር እስከሆነ ድረስ ምንም እንኳን የምወደውና የምፈልገው ነገር ቢሆን አላደርገውም ብሎ መቁረጥ ነው፡፡ 1ቆሮ 8፡13
4. አዎን ለአንዱ ሃጥያት የሆነ ለሌላው ላይሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ ቁ14 የሚናገረው ይህንኑ ሃሳብ በመደገፍ ነው፤ ማለትም አንድን ነገር አማኝ ከማድረጉ በፊት በሃሳቡ ትክክል መሆኑን መወሰን አለበት፤ ካልሆነ ግን ከእምነት ስላላደረገው ሃጥያት ይሆንበታል፡፡
5. በቁ14 ጳውሎስ ምግብን በተመለከተ እውነቱ ምን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል ነገር ግን በቁ15 ላይ ይህንን እርግጠኛ የሆነበት እውነት ለሌሎች ማሰናከያ እስከሆነ ድረስ ለፍቅር ሲል ባወቀው እውነት ከመመላለስ ይቆጠባል ማለት ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ተግባር ፍቅርን በተጨባጭ መንገድ የማሳያ ግልጽ መንገድ ነው፡፡ ‹‹በፍቅር አልተመላለስክም››
6. እውነትን እያወቁ ሌላውን ላለማሰናከልና ወይም ለማነጽ ሲባል መብትን በመተው መኖር ማለትም በፍቅር መመላለስን ነው የሚጠቁመን፡፡ ይህ አይነቱን አኗኗር አገልግሎት ሆኖ ነው በዚህ ክፍል የተነገረው፤ ምክንያቱም ሰዎችን ቃሉን አስተምረን ልናንጻቸው እንችላለን ወይም ደግሞ በአኗኗራችን ምሳሌነት ማነጽ እንችላለን፡፡
7. እነዚህ ሁለት ነገሮች ሰላምና እርስ በእርስ መተናነጽ ናቸው፡፡ አንዱ ለሌላው የራሱን መብት እየተወ መመላለስ ከጀመረ መፈራረድና መከራከር ስለማይኖር ሰላም ይበዛል፤ ብርቱው ደካማውን እርሱ የደረሰበት ደረጃ አንጾ ካደረሰው ያ የታነጸው ደግሞ ለሌላው መታነጽ በመሆን ይህ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚቀጥል በረከት ይሆናል ማለት ነው፡፡
8. በሮሜ 14፡1 አከራካሪ በመባል የተጠቀሱት ናቸው፡፡

# <u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>

## <u>ጥናት ሰላሳ አንድ(ሮሜ 15፡1-13)</u>

1. ጳውሎስ ራሱን የሚመድበው ከብርቱዎቹ ሲሆን ይህም በ15፡1 ላይ እኛ ብርቱዎች በማለቱ ያሳያል፡፡ በሮሜ14፡14 ላይ የተናገረው በክርስቶስ የተገኘው የአስተሳሰብ ነጻነት ላይ ያለው መረዳት ነው፡፡
2. ከራስ ይልቅ ለሌላ ማሰብን ያስተምረናል፡፡ ለባልንጀራ ማድረግ የምንችላቸው ሶስቱ ነገሮች፤ ባልንጀራን ማነጽ፤ ባልንጀራን መጥቀምና ባልንጀራን ደስ ማሰኘት ናቸው፡፡
3. የመጽናናጽ ምንጭ ሆነው የተጠቀሱት ሁለቱ፤ ቅዱሳት መጻህፍትና እግዚአብሄር አምላክ ናቸው፡፡
4. ይህ ‹‹ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ›› የሚለው ሃስብ በቁ3 ላይ የተነገረውን ክርስቶስ ራሱን ደስ ስላላሰኘ በእርሱ ፈለግ የመመላለስን ሃሳብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡
5. በነዚህ ቁጥሮች መሰረት የአንድነት መንፈስ የሚገኘው ክርስቶስን ስንከተል ማለትም ራሳችንን ደስ ከማሰኘት ይልቅ ለሌሎች መታነጽ፤ ለሌሎች ጥቅምና ለሌሎች ደስታ ስንኖር ነው፡፡
6. የአንድነት መንፈስ የሚያካትታቸው በቁ6 መሰረት አንድ ልብና አንድ አፍ ሲሆኑ ይህም ማለት የሚስማማው አንደበታችን ብቻ ሳይሆን የልባችንም አንድ መሆንና መስማማት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡
7. አንደኛው ከራስ ይልቅ ባልንጀራን ደስ ማሰኘት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሌሎችን ባሉበት ደረጃ መቀበል ናቸው፡፡
8. በነዚህ ቁጥሮች የተሰነዘረው ሃሳብ ለምናደርጋቸው ማናቸውም ነገሮች ሁሉ ምክንያታችንና ግባችን የእግዚአብሄር ክብር ሊሆን እንደሚገባው ነው፡፡ ባልንጀራችንን ደስ ብናሰኝ፤ የመንፈስ አንድነት ቢኖረን፤ እርስ በእርስ ብንቀባበልም ሆነ ሰዎችን ብናገለግል የልባችን ፍላጎት እግዚአብሄር ይከብርበት ዘንድ ሊሆን ይገባል፡፡
9. እያንዳንዱ ተካፋይ የራሱ የሆነ ሃሳብ እንዲሰነዝር ማበረታታት ይቻላል፡፡

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሰላሳ ሁለት (ሮሜ 15፡14-32)

1. በበጎነት የተሞሉ እንደሆኑ፤ በእውቀት የተሞሉ እንደሆኑና አንዱ ሌላውን ለመምከር ብቃት ያላቸው መሆኑን ይነግራቸዋል።
2. ያገልግሎት ትምክህት እግዚአብሄር ብቻ እንደሆነ፤ ስላገልግሎት መናገር ካስፈለገ ክርስቶስ በኛ ስለሰራው እንጂ እኛ ስለሰራነው ነገር መሆን የለበትም፤ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ብቻ ነው፤...
3. ደብዳቤውን ሲጽፍ ከቆሮንቶስ ስለነበረ ቤተ ክርስትያን ተመስርቷል የወንጌልን አደራ የሚቀበሉ ቅዱሳን ስላሉ አካባቢው በእነርሱ ይደረሳል ማለቱ ነው።
4. እነዚህ ሁለት ክፍሎች አማኝ የረጅምና የአጭር ጊዜ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ ዕቅድ በማውጣት መኖር እንደሚችልና ይህ እቅድ ደግሞ ለእግዚአብሄር ፈቃድ አልፎ መሰጠት እንደሚኖርበት እንማራለን። ሮሜ1፡9-10፤ ያዕ 4፡15
5. መንፈሳዊ በረከት ላካፈሉን ሰዎች ሥጋዊ በረከትን ማካፈል ትልቅ ነገር ሆኖ ሊታየን አይገባም። ቁ27
6. ጳውሎስ የጀመረውን ነገር ሳይቋጥር ወደ ሌላ የሚዘል ሰው አይደለም። ወንጌልን ማሰራጨት ዋና ዕቅዱ ቢሆንም የጀመረውን ለድሆች ገንዘብ ማድረስ መከናወኑን ማየትም ከዚያ አሳንሶ አያየውም።

# <u>ለመሪው የተዘጋጀ</u>

## <u>ጥናት ሰላሳ ሶስት (ሮሜ 16፡1-16)</u>

1. ፌቤን በክንክራኦስ ቤተክርስትያን ውስጥ አገልጋይ እንደሆነች፤ ለጳውሎስ ድጋፍ እንዲሁም ለሌሎችም ድጋፍ እንደነበረች እናያለን። ጳውሎስ በአክብሮት የሚመለከታት የክርስቶስ አገልጋይ እንደነበረች እንመለከታለን።
2. ለቅዱሳን ተገቢ የሆነ አቀባበል የሚለው በተለይ በጌታ ስራ ለሚደክሙ በሙሉ ደስታና በአክብሮት የሚደረግ አቀባበል ነው። ፊሊ 2፡29-30
3. ከጳውሎስ ጋራ የጌታን ሥራ የሚሰሩ ናቸው፤ ለጳውሎስ ሲሉ ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠዋል፤ የአህዛብ አብያተክርስትያናት ያመሰግኗቸዋል፤ በቤታቸው ቤ/ክ አለ።
4. ከጳውሎስ ጋራ ታስረው ነበረ፤ በሐዋርያት መካከል ስመጥሮች ነበሩ፤ በክርስቶስ በማመን ጳውሎስን ይቀድሙታል። ይህ ማለት በጌታ መቆየታቸው እድሜ የመቁጠር ነገር ብቻ ሳይሆን ለወንጌል ሥራ በመጋደልና መልካምን ሥም በወገኖች በማትረፍ የታወቁ እንደነበሩ እንገነዘባለን።
5. እነዚህ የተዘረዘሩት ሰዎች አብዛኛዎቹ በጌታ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚለፉና የሚደክሙ ዓይነት ሰዎች ናቸው።
6. ከብዙዎች መሃል ሰዎችን በሥም እየጠሩ ማመስገን፡ ለመታበይ ይዳርጋቸው ይሆናል፤ ሌላው ደግሞ የሚደክሙ ነገር ግን ሥማቸው ሳይጠራ ሊረሱ የሚችሉ ሊኖሩ ይችላል።ጳውሎስ አደጋውን ሳይረዳ ቀርቶ ሳይሆን ከጉዳቱ ጥቅሙ መብለጡን ተረድቶ ነው ለማለት ይቻላል።
7. የጳውሎስ አገልግሎት በአንድ ሰው ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን የቡድንና የህብረት አገልግሎት ላይ ያተኮረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።
8. ኢየሱስም ሁለት ሁለት እያረገ መላኩና ከራሱ ጋራ የሚሰሩ አስራ ሁለቱን ከዙሪያው አድርጎ ለአገልግሎት ማዘጋጀቱ ተመሳሳይ አመለካከት እንዳቸው ያሳየናል።
9. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ያካፍል።

# ለመሪው የተዘጋጀ

# ጥናት ሰላሳ አራት (ሮሜ 16፡17-27)

1. መለያየት የሚፈጥሩና የተማሩትን ትምህርት በመቃወም በጉዟቸው መሰናክል የሚያደርጉ ናቸው። የሚያስጠነቅቃቸውም እንዲጠነቀቁና ከእነርሱ እንዲርቁ ነው።
2. ስለነዚህ ሰዎች ልናውቅ የምንችላቸው፡ መለያየት የሚፈጥሩ፤ ትክክለኛ ትምህርትን የሚቃወሙ፤ ለአማኞች ጉዞ መሰናክል የሚሆኑ፤ ራሳቸውን የሚያገለግሉ፤ በለሰለሰ አንደበትና በሽንገላ የሚናገሩና የሚያታልሉ ናቸው።
3. ሮሜ 15፡3-6 ያለው ክፍል ለሌሎች መኖርን ከየሱስ ስንማር በመሃላችን አንድነትና ህብረት ይመጣል በሮሜ 16፡17-20 ደግሞ ለራሳችንና ለሆዳችን ስንኖር መለያየትና መከፋፈል በመሃላችን ይዘራል።
4. ለወንገል ከመታዘዛቸው ሌላ ለበጎ ነገር ጥበበኞችና ለክፉ ነገር የዋሆች እንዲሆኑ ይመክራቸዋል። ኢየሱስ እንደ እባብ ብልሆች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ ያለው ቃል ከዚህ ጋራ ተመሳሳይ ነው። ማቴ 10፡16
5. በሮሜ1፡8 ማመናቸው ተረጋግጧል፤ በ16፡19 መታዘዛቸውን ተመልክተናል፤ ስለዚህ በ16፡25 መሰረት የዘላለማዊውን አምላክ ትዕዛዝና ፍላጎት ፈጽሟል ማለጽት ይቻላል።
6. ምንም እንኳን ሰዎች ለመከፋፈል መጠቀሚያ ቢሆኑም የእግዚአብሄርን መንጋ ለመበታተንና ለመክፋፈል ከበስተጊላ የሚያቀነባብረው ሰይጣን ስለሆነ ነው።
7. በዚህ ክፍል የሚዘረዝራቸው ሰዎች አብረውት ከእርሱ ጋራ ያሉ አማኞች ናቸው። ከሚያስተዋውቅባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ፡ አብሮኝ የሚሰራ፤ በመልካም መስተንግዶው ደስ የሚያሰኝ፤ ወንድማችንና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከዚህ የምንማረው በርቀት ያሉትን ብቻ ሳይሆን በቅርባችን ሆነው አብረውን የሚደክሙትንም መርሳት እንደማይኖርብን እንማራለን።
8. የቅዱሳን ህብረት፤ አንድነትና ሰላም በእግዚአብሄር አይን እጅግ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ነገር ስለሆነና መለያየትንም የሚጠላ ሲሆን ለዚህም ኤፌ4፡4-6፤ ምሳሌ 16፡19፤ 1ቆሮ 12፡25 ትንና ሌሎችንም ክፍሎች ማየት ይቻላል።
9. እያንዳንዱ የየራሱን ሃሳብ እንዲገልጥ ማበረታታት።